

“ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ ” (ሉቃ1 ፡ 19)

# ትንሣኤ



መልአኩ ቅ/ ገብርኤል ለድንግል ማርያም “እነሆ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ ” በማለት እንዳበሠራት

27

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 28 ታኅሣሥ/፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

“ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ “ትንሣኤ” ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ለአንድ ቤት አንድ ሥርዐት | ፪ |
| ገብርኤል ማን ነው? | ፫ |
| ፈላጊና ተፈላጊ ሳይገናኙ መሸ | ፬ |
| ነፍሴ ተመከረ | ፭ |
| የሃይማኖት ዐምድ | ፮ |
| የኢትዮጵያውያን ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች | ፯ |
| የወጣቶች ዐምድ | ፰ |
| የዐራት ቀን ሴሚናር በባሕር ዳር | ፱ |
| ምን እንርዳዎ? | ፲ |
| የሴቶች ዐምድ | ፲፪ |
| ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች | ፲፫ |
| ይህን ያውቁ ኖሯል? | ፲፬ |
| ዜና ሀገረ ስብከት | ፲፭ |
| ዜና አብያተ ክርስቲያናት | ፲፭ |
| የጤና ዐምድ | ፲፯ |
| ሊቃውንቶቻችን | ፲፰ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፳ |
| ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ | ፳፩ |
| የመጽሐፍ ቅዱስ ዐምድ | ፳፫ |


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ወንጌልን የጻፉ አራት ወንጌላውያን ሲሆኑ ከእነዚህ መሃከል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለማርቆስና ለዮሐንስ ጽላት ተቀርፆ ቤተ ክርስቲያን ሲታነጽላቸው ለማቴዎስና ለሉቃስ ጽላት በስማቸው ለምን አልተቀረጸም?

ወ/አማኑኤል
አዲስ አበባ

● ማቴዎስና ሉቃስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ታላቅ ክብር አላቸው ፤ ለምሳሌ ማቴዎስ በጥቅምት 12 ሲከበር ሉቃስ በጥቅምት 22 ቀን ይከበራል ። ነገር ግን በስማቸው ጽላት ስለመቀረጹና ቤ/ክርስቲያን ስለመታነጽ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ጠይቀን ነበር ሆኖም እርግጠኛውን አልነገሩንም እርግጥ በተደራቢነት እንደሚኖሩ ተነግሮናል በስማቸው የታነጸ ቤተ ክርስቲያን መኖሩን የሚያውቅ ቢኖር ቢጽፍልን እጅግ ደስ ይለናል ።

★★★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

“የጤና ዓምድ” በሚለው ርእስ ስለ አቶ ጌታቸው ደስአለኝ የተገለጠውን ለማየትም ሆነ ነገሩን ለማረጋገጥ እንደሚቻል ተጠቅሶአል ። በዚህ መሠረት ለመረዳት ስለምፈልግ አድራሻቸውን እንድትጠቁሙኝ እጠይቃለሁ ።

ዝናብዋ ገላው
አዲስ አበባ

● ዝናብዋ ገላው መጽሔታችንን በመከታተል ይህን ጥያቄ ስለጻፉልን እናመሰግንዎትአለን። አቶ ጌታቸው ደስአለኝን ለማየትና ሁኔታቸውን ለማረጋገጥ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 12-03-89 በመደወል ቀጠሮ ይዘው ማየትና ማነጋገር ይችላሉ ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ የከበረ ሰላምታዬን እያቀረብኩ በዚህ ደብዳቤ ላይ ያቀረብኩትን ጥያቄ እንደምትመልሱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ ።

መስከረም 10 ቀን 72 ዓ.ም. በደብረ ፍሥሐ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲ ውስጥ እንዳለሁ አንድ መምህር አበቅቴ ሲያስሙ አዳምጥ ነበር ። ይኸውም ከሚናገሩት ቃል ጥቂቱ በግዕዝ ሲሆን አንዳንድ ጊዜም እንደ ሂሳብ ዓይነት የመደመርና የመቀነስ ፣ የማካፈልም መልክ ይዘው ነበር በግዕዝ ከሚናገሯቸው ቃላቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ለምሳሌ አበቅቴ ፣ መጥቅዕ ... ወዘተ

ይህም ሆኖ ሳለ በመጨረሻ አጽዋማትና በዓላት በትክክል የሚውሉበትን ወራትና ቀን ተንትነው መናገር ጀመሩ

በዚያን ጊዜ እኔ በሀሳቤ ይኸን የመሰለውን የአበቅቴ አወጣጥ ትምህርት በጣም ጠቃሚ እንደመሆኑ መጠን ለምን እያንዳንዱ ሰው (ከኔ ጀምሮ) እንዲማር ወይም እንዲመራመር አይደረግም ለዚህስ የተዘጋጀ መጽሐፍ አለወይ? ከሌለስ ለምን አይዘጋጅም?

ሀበነ ሚካኤል
ከፍቼ

● ሀበነ ሚካኤል ስለ ጥያቄዎ እናመሰግናለን ። በቤተ ክርስቲያናችን የተዘጋጁ የቁጥር መጻሕፍት አሉ ። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ኦ.ተ.ሐዋርያዊ ድርጅት የድርሰት ክፍል ተዘጋጅቶ በ1962 ዓ.ም. የታተመ አቡሻህር የተባለ መጽሐፍ አለ ። ይህን መጽሐፍ ቅ/ሥላሴ ቤ/ክርስቲያን ፊት ለፊት ባለችው ሱቅ ማግኘት ይቻላል ዋጋውም 4 ብር ብቻ ነው ። ከዚህም ሌላ “መርሀ አዝማን” የተባለ በመምህር ኪዳነ ማርያም ገ ሕይወት ተዘጋጅቶ ታትሞአል ። ይህም በትንሣኤ ዘጉባኤ መጻሕፍት መሸጫ መደብር ይገኛልና ገዝቶ ማንበብ መማርና መመርመር ይቻላል ።

✶✶✶

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ የሚገኙ በቅርብ ጊዜ የተመሠረቱ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በዲፕሎማና በዲግሪ የሚያስመርቁባቸው ኮሌጆች ሲኖሯቸው አንጋፋ ለሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን በዲፕሎማና በዲግሪ ካህናትን የምታስተምርበት ኮሌጅ ለምን የላትም?

ዲ/ዘለዓለም ቢረሳው
አዲስ አበባ

● ዲያቆን ዘለዓለም ቢረሳው ስለ ጥያቄዎ እናመሰግናለን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ካህናትን በዲግሪ የምታስመርቅበት መንፈሳዊ ኮሌጅ መሥራት ትችል ነበር ፤

ግን ስለዚህ ጉዳይ የሚያስቡ ያሉ አይመስለንም ለጊዜው መሥራት ባትችልም እርስዎ ከጠቀሰዋቸው አብያተ ክርስቲያናት ጋር ተባብራ ካህናቶችዋን ለማሠልጠን ብትሞክር መልካም ይሆንላታል ። ይህን ለማለት የደፈርነው እስካሁን ድረስ ልጆችዋን ወደ ውጭ ልካ የምታሠለጥነው በ“ሁለት ባሕርይ” ባዮች ኦርቶዶክሳውያን በካቶሊካውያንና በፕሮቴስታንቶች ኮሌጆች ውስጥ ስለሆነ ነው። እንዲህ ከሆነ እዚህ ካሉት ጋር የማትተባበርበት ምክንያት አይገባንም። ነገሩን ግልጥ ለማድረግ ያህል፦ በምዕራብ ጀርመን በሚገኘው የሉተራን ኮሌጅ ልጆችዋ ይማራሉ ለክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ብለው በሚያምኑ በራሺያና በግሪክ ኮሌጆች ልጆችዋ ይሠለጥናሉ ።በሮምና በአየርላንድ በሚገኘው በካቶሊክ ኮሌጆች ልጆችዋን ልካ ባሁኑ ጊዜ ታስተምራለች። ስለዚህ የራስዋ የሆነ የካህናት ማሠልጠኛ ለማቋቋም ብታስብ ችግር አይኖርም ነበር ግን ለመሥራትም ሆነ በሀገር ውስጥ ካሉት ጋር ለመተባበር ብታስብበት መልካም ነው እንላለን ።




www.ethiopianorthodox.org

## ርዕሰ አንቀጽ

# ለአንድ ቤት አንድ ሥርዓት

ፍጥረት ሁሉ የራሱ የሆነ ሕግና ሥርዓት አለው ፡ እያንዳንዱ ሂደትና እንቅስቃሴ በራሱ ሥርዓት ይመራል ፡ አንድ ዓይነት የሆነው ፍጥረት ሁሉ በአንድ ሥርዓት ይንቀሳቀሳል የአንዱ ወገን ከሌላው ሥርዓት የተለየ ይሆናል ፡ ተፈጥሮው አንድ አይነት ከሆነ ግን የተለያየ የሂደትና የእንቅስቃሴ ሥርዓት አይኖረውም ፡ በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የተፈለገ የተፈጥሮን ሕግጋትና ሥርዓት አይደለም ምክንያቱም ተፈጥሮን ለመመርመር ሌሎች ሊቃውንት አሉበትና ነው ።

በዚህ ርእስ ለመግለጥ የተፈለገው በአንድ ጠባቂ (ፓትርያርክ)ስለምትመራው ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ የተመሠረተች በሐዋርያትና በ318 ሊቃውንት ሥርዓት የጸናች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት ። ታዲያ እውነቱን እንድንነጋገር ከተፈቀደ በብዙ የተለያየና የተዘበራረቀ ሥርዓት መኖሩ አይካድም ፡ አንዲት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሆነችና በአንድ ሲኖዶስ የምትመራ ከሆነ ሥርዓትዋስ ለምን አንድ አይሆንም? የተለያየው ሥርዓት የቱ ነው የተባለ እንደሆነ 1ኛ/ የቅዳሴ ሰዓት ፡ ከሩቅ ሳንሄድ በአዲስ አበባ ያሉትን አብያተ ክርስቲያን የቅዳሴ ሰዓት ብንመለከት በእሁድ ቀን በአንድዋ ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ቅዳሴው በ12 ሰዓት ወይም ከዚያ ቀደም ብሎ ሲጀምር በሌላዋ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ሰዓት ይጀመራል ታዲያ ሥላሴ "አሐዱ" ሲባል ገብርኤል "እግዚኦ" ሲባል ይሰማል ሁኔታው ተመልካችን ያስደንቃል ።

2ኛ/ ጾም ባልሆኑ በዘወትር ቀናት በአንዱ ቤተ ክርስቲያን ጠዋት ሲቀደስ በሌላው ውሎ ይቀደሳል ፡ ይህ ለምን ይሆናል ስምምነት ቢደረግና በአንድ ሰዓት ቢወሰን ፤

3ኛ/ የአጽዋማት ሁኔታ ነው "ጾመ ነቢያት" እየተባለ የሚጠራውን የኅዳር ጾም አንዳንዶቹ አብያተ ክርስቲያናት በኅዳር 15 ቀን ሲጀምሩ ሌሎች በ16 ይጀምራሉ የመምሬ እገሌ የንስሐ ልጆች ሲጾሙ ሲውሉ የመምሬ እገሌ የንስሐ ልጆች ቅበላ አድርገው ይውላሉ ፡ እንደዚሁም በየአራቱ ዓመት የልደት በዓል አከባበር ሁኔታ ታላቅ መለያየትን ሲፈጥር ይታያል ለምሳሌ በዘመነ ዮሐንስ ልደት 28 ቀን ማክሰኞ ሲሆን በማግስቱ ረብዕ በአንዱ ቤተ ክርስቲያን ጠዋት ሲቀደስ ሌላው ውሎ ይቀድሳል ሊቃውንቶቻችንም ይህን የመሳሰለውን ሥርዓትና የእምነት መገለጫ እንዲያስረዱ ሲጠየቁ የአንዱ ሊቅ አባባል ከሁለተኛው የሁለተኛው ከሦስተኛው የተለየ ይሆናል ፡ በዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች የሆኑት ምእመናን ግራእየተጋቡ ናቸው ።

ቤተ ክርስቲያንዋ አንዲት መሪዋም አንድ ፓትርያርክ ከሆነ በውስጥዋ ለምን የተለያየ ሥርዓት ኖረ? ሊቃውንትስ ለምን የተለያየ አስተያየት ይሰጣሉ ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ፡ የቅዳሴ ሰዓታችን ፡ ሥርዓተ ጾምን የሚወስንና እምነታችንን የምናስተምርበት ሊቃውንቱ የተስማሙበትና በሲኖዶስ የተወሰነ መመሪያ ስለሌለ ነው የሚል ይሆናል ፡ ትክክለኛ አባባል ነው ታዲያ እስከ መቼ ነው ? በተለያየ ሥርዓትና አነጋገር የምንኖረው? "እርስ በርስዋ የምትለያይቤት አትጸናም" ይላል ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት ክርስቶስ ። አዎ መለያየት ከአለ መጽናት አይኖርም ፡ ስለሆነም ቤተ ክርስቲያናችን እንድትጸና እምነታችን እንዲስፋፋ አንድ ሥርዓት እንዲኖረን ያስፈልጋል ።

ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ በጉዳዩ ቢያስብበትና ሊቃውንቱን ሰብስቦ በማነጋገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አንድ የሚያደርግ ሥርዓትና እምነትዋንም የምታስተምርበት የተወሰነ ትምህርተ መለኮት በሲኖዶስ ጸድቆ ቢመጣ መምህራን ከመለያየትና ከመሳሳት ምእመናን ግራ ከመጋባት ይድናሉ ብለን እናምናለን ።



# ገብርኤል ማን ነው ?

ገብርኤል ማለት በዕብራይስጥ "የአምላክ ሰው ወይም አምላክ ራሱን ኃያል አደረገ" ማለት ነው ። በአምስተኛው ምእትዓመት የነበረው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ደግሞ " ገብርኤል ማለት ሰውና

/ሄኖክ 10 ፡ 9 ፡ 20 1-8 ፡ 9 ፡ 11 ፡ 6-9 /

በሐዲስ ኪዳን፦— ገብርኤል በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም መልእክተኛ ነው። /ሉቃ 1 ፡ 19 / ስለዚህም ከመላእክት ሁሉ የበለጠ ባለሞአልነት



ሰዎችን ለመርዳት የሚላከው ቅ/ገብርኤል

አምላክ እንደዚሁም የአምላክ ልጅ" ማለት እንደሆነ ተርጉሟል። በመጽሐፍ ቅዱስበ ስም ተለይተው ከተጠቀሱ ሁለት መላእክት መካከል አንዱ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ሲሆን ሁለተኛው ቅዱስ ገብርኤል ነው ። ገብርኤል በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት ለሰው ልጆች ብዙ ሥራን ሠርቶአል።ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን ፡—

ሀ / ለዳንኤል ራእይ ተረጐመለት /ዳን 8፡ 16 /

ለ / ዳንኤልን አጽናናው፣ ጥበብንና ማስተዋልን ገለጠለት /ዳን 9 ፡ 21

ገብርኤል በሄኖክ መጽሐፍ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ ሆኖ ከመጠቀሱም ሌላ የተግሣጽ መልአክ እንደሆነ ተገልጦአል ።

እንዳለው እንመለከታለን ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ካረጁ በኋላ ልጅ እንደሚወልዱ የምሥራች ነገራቸው ። /ሉቃ 1፡11-22 ለእመቤታችን ለድንግል ማርያምም አምላክን በሥጋ እንደምትወልድ ያበሠረ ይኸው ገብርኤል ነው /ሉቃ 1 ፡ 26-38 / ከዚህም የተነሣ ገብርኤል የደስታ የሰላምና የምሥራች መልአክ በመባል ይጠራል ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ኦ . ተ . ቤ/ ክርስቲያን ሊቅ ስብሐት ለአብ ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም በደረሰው መዝሙር "ድንግል ሆይ ደስተኛ ከሆነው ገብርኤልና እንደ እንቺ ርኅሩኅ ከሆነው ሚካኤል ጋር ነይ" ሲል ገብርኤል የደስታ መልአክ መሆኑን ገልጦአል ።

ሊቃውንት፦— በመጽሐፍ ቁዱስ በሰልፍ ሜዳ ላይ ለእግዚአብሔር ሰዎች የታየው መልአክ ሚካኤል እንደሆነ ይተረጉማሉ ነገር ግን ራእይን ለመተርጐም ጥበብንና ማስተዋልን ደስታንና ሰላምን ለማብሰር ወደ እግዚአብሔር ሰዎች የተላከው መልአክ ገብርኤል መሆኑን ያምናሉ ።

እንግዲህ በዚህ መሠረት ለኢያሱ በጦር ሜዳ ላይ ሰይፍ ይዞ የታየ በለኪሶን ሜዳሰና ከሬምንና ሠራዊቱን የተዋጋ እስራኤላውያንን ከጠላቶቻቸው ከግብጻውያን ያዳነ ሚካኤል ነው። ይህም ሀሳብ በራእይ 12፡7 ላይ ተደግፎአል ።

ገብርኤል ደግሞ፦—አጋር ከልጅዋ ከእስማኤል ጋር በበረኃ ተጥላ ስታለቅስ ተገልጦ አጽናናት ልጅዋ ታላቅ ሰው እንደሚሆን አበሠራት መካን ለነበረችው ለሶምሶን እናት ልጅ እንደምትወልድ የምሥራች ነገራት ። ይህን የመሰለው አስደሳች ተግባር ሁሉ የገብርኤል እንደሆነ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ውስጥ የተገለጠ መሆኑን በላይ አስረድተናል ።

ከዚህም ጋር ያለ ስም የእግዚአብሔር መመልአክ በመባል የሚጠራው ሁሉ አንዳንድ ጊዜ ለሚ ካኤል ሲነገር በሌላ ጊዜ ደግሞ ለገብርኤል ይነገራል ። ለምሳሌ በተረፈ ዳንኤል ውስጥ ሠለስቱ ደቂቅ (ሦስቱ ወጣቶች) በእሳት ጉድጓድ በተጣሉ ጊዜ ከእሳቱ ያዳናቸው የእግዚአብሔር መላክ ቅዱስ ገብርኤል ነበር ። እነሆ በየዓመቱ ታኅሣሥ 19 ቀን የሚከበረው በዓል ገብርኤል ሦስቱን ወጣቶች ከእሳት ነበልባል ማዳኑን ለማስታወስ ነው ። ዛሬም ቢሆን ቅዱስ ገብርኤል በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም መልአክ እንደመሆኑ መጠን ለአማኞች ምሕረትን ይለምናል ያዘኑትን ያጽናናል። ደስታንና የምሥራችን ይናገራል እንደ ሠለስቱ ደቂቅ (ሦስቱ ወጣቶች) በእምነት ጸንተውና በእምነት ሆነው ለሚለምኑ ሁሉ ልመናቸውን ወደ እግዚአብሔር ያደርሳል የልመናቸውንም ውጤት ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ያስገኛቸዋል ። ይህንም ለማረጋገጥ በየዓመቱ በቁልቢ ገብርኤልና በኢሊ ገብርኤል (ጋሞ ጎፋ) የሚደረገውን ተአምር መመልከቱ ብቻ ይበቃል። ምናልባት በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል አማካኝነት የሚደረገውን ተአምር ለማመን የሚቸግራቸው

ወደ ገጽ ፮ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ክርስቲያናዊ ሕይወት

# "ፈላጊና ተፈላጊ ሳይገናኙ መሽ"

በዱሮ ዘመን አንድ ትዳር ፈላጊ ለጓደኛው "ሚስት ፈልግልኝ" ይለዋል "እንዴት ያለች ሴት ልፈልግልህ" አለ ተጠያቂው ጓደኛ. ጠያቂውም መልሶ 1. ብዙ ገንዘብ ያላት
2. ርስት ያላት
3. የሚያኮራ ወገን ያላት
4. ባለሙያ የሆነች
5. መልኳ በጣም ቆንጆ የሆነ
6. በጠባይዋ ተናገራ የማታስቀይም ፣ ልበ ሰፊ ነገር አሳላፊ የሆነች ይለዋል ባለፈውና በወደቀው ሥርዓት የመተሚጩት ወይም የመፈላለግ መመሪያ እንዲህ አይነት ነበርና ነው ። ተጠያቂውም "እንዲህ ያላችውንስ ባገኝ ለሌላ በልሰጠኋትም ነበር አለው ይባላል ። በአሁን ጊዜ ደግሞ ትዳር ፈላጊ ወጣቶች የሚመሩበት ከበፊቱ ለየት ያለ መመሪያ አውጥተዋል ይኸውም

1. የተማረችና ጥሩ ደመወዝ ያላት
2. የት ዋልህ የት አደርህ በማለት ቁጥጥር የማታበዛና የማትቀና
3. ለቤት መሰናዶና ለምግብ ዝግጅት የአመራር ስልት የምታውቅ
4. የገንዘብ አያያዝና የልጆች አስተዳደግ እንዴት እንደሆን የተረዳች
5. በመልክዋ ፣ በደም ግባትዋና በንግግር ለዛዋ የምታስደስት
6. የባልዋ ሕይወት የራስዋ ሕይወት መሆኑን ያወቀች መሆን አለባት ይላሉ ።

ወጣት ሴቶችም እንዲሁ የትዳር ጓደኛ ለማድረግ የሚፈልጉት ወንድ ምን አይነት ሰው መሆን እንዳለበት ሲገልጡ፡-

1. ጠጥቶ የማይሰክር
2. ሲጋራ የማያጨስ
3. ውጭ የማያመሽና ገንዘብ የማያባክን
4. ደመወዙን በሞላ አምጥቶ ለሚስቱ የሚያስረክብና ለሚያስፈልገው ሁሉ ከባለቤቱ ጋር እየተመካከረ የሚያወጣ ፣
አንዳንድ ወንዶች ሚስት ያገቡና አንድና ሁለት ልጆች ከወለዱ በኋላ ሚስቶቻቸውን ይጠላሉ ። ያልወለደችውንና ሕፃን በማቀፍ ያልተጉሳቆለችውን ይፈልጋሉ። ስለዚህ እንዲህ የማይሆን ሚስቱንና ልጆቹን የማይጠላ አስመስላ ፣ አሳክላ የወለደችለትንና የቃል ኪዳን ሚስቱን በሌላ የማይለውጥ የአንዱን ልጅ ይዛ ሌላ ወንድ ማግባት ለትዳር በጣም አስቸጋሪ ነው ። ስለዚህ ከወለደ በኋላ ችግሩን ችግር ደስታውንም ደስታ አድርጎ ሁሉን በሁሉ ታግሦ የሚኖር እንጂ በሆነ ባልሆነ የሚጨቃጨቅና የሚፈታ መሆን የለበትም ይላሉ ።

መመሪያውን አተኩረን ስንመለከት ወጣቶቹ ሴቶች የሚከተሉት መመሪያ በአግባቡ የሚነገርና ተቀባይነትም ያለው ነው፤ የወንዶች መመሪያዎች ግን ጥቂቶቹ ተሟልተው የማይገኙና ሊቀርቡም የማይገባቸው ሆነው ይታያሉ ። ታድያ "ካልታረደ አይታይ ስባቱ ካልተነጋገሩ አይገኝ ብልሃቱ" እንደሚባለው ሁሉ ወጣቱና ወጣትዋ ክራይቴርያውን /መመሪያውን/ ብቻ ከማውጣት ከማውረድ ይልቅ ፈላጊና ተፈላጊ ተገናኝተው ቢነጋገሩ አብዛኞዎቹ ይግባቡና ትዳር ይመሠርቱ ነበር ። ይሁን እንጂ ክራይቴርያው /መመሪያው/ ስለበዛ ይህን የሚያሟላ፣ ይህን የምታሟላ ካልሆነ አላደርገውም ሲባባሉ ዕድሜ እየተጓዘ ወደእርጅናው አፋፍ ደርሰው ይታያሉ ። ከሞላ ጎደል ክራይቴርያውን /መመሪያውን/ ያሟላሉ የሚባሉ ቢኖሩም ባለመተዋወቃቸውና ባለመገናኘታቸውም ፈላጊና ተፈላጊ ሳይገናኙ ከሽምግልና ዕድሜ ይደርሳሉ ። ከዚህ ላይ አንድ ትዳር ፈላጊ የፈለጉትን ትዳር ሳይመሠርቱ ሽምግለው የተናገሩትን እናስታውሳለን ፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን አባት ትዳር ፈላጊውን አዛውንት "እስከ አሁን ለምን በትዳር አልተወሰንህም" ብለው ቢጠይቋቸው ትዳር ፈላጊው አዛውንት ሲመልሱ "እኔ በምዕራብ ወይም በሰሜን በር ገብቼ እባክህ ፈጣሪዬ ለእኔ የምትሆን ስጠኝ በማለት ጸሎት ለእግዚአብሔር አቅርቤ ዕንባዬን አፍስሼ እመለሳለሁ፣ እርስዋም እንዲሁም በደቡብ በር ገብታ የምትፈልገውን የትዳር ጓደኛ እንድታገኝ ጸሎት አድርሳ ዕንባዋን አፍስሳ ትመለሳለች። ይሁን እንጂ የእርስዋ ዕንባና የዕኔ ዕንባ አልተገጣጠመም መሰለኝ ይኸው ስንፈላለግ ጊዜው አለፈብን "አሉ ይባላል። እንዲህ ከሆን ፈላጊና ተፈላጊ ሲገናኙ የሚችሉበት ዘዴው ምን ይሆን? ቦታውስ የት ይሆን? የሚል ጥያቄ በአንባቢዎች አእምሮ ይቀረጻል፣ መልሱን ለማግኘት ጥበብ፣ ትዕግሥትና ጸሎት ያስፈልጋል።

ባለፈው ዘመን ወጣቶች ለመተያየትና እርስ በርሳቸው ለመተዋወቅ፣ የትዳር ጓደኛንም ለመምረጥ የሚሞክሩበት የመስቀልና የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ጊዜና ቦታ እንደ ነበረ አዛውንቶች ይናገራሉ ። በዚህ መሠረት አንድ ወጣት የትዳር ጓደኛውን ለመምረጥ የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ዕለት በዓሉ ወደ ሚከበርበት ቦታ ይሄዳል ።

እንዲት አልባሌ ወጣት በትውስት ልብስ አጊጣ ፣ ከርዳዳ ጸጉሯን አበጥራ፣ ሞጭሟጫ ዐይኗን ተኳኩላ ይመለከታል፣ ለጊዜው ደህና መሰለችውና ትሆነኛለች ብሎ ምርጫውን በእርሷ ላይ አተኮረ ። ጋብቻው ተፈጸመ የሙሽርነታቸው ጊዜ ተፈጽሞ ከጫጉላ ሲወጡ የተፈጥሮ መልኳ ተከሠተ ከመልኳ አለማስደሰት የጠባይዋ መክፋት አስቸገረው ። በዚህ ጊዜ ወጣቱ ምርጫው ትክክል አለመሆኑን ተረድቶ ከጸጸት ላይ ወደቀ ይህ በዚህ እንዳለ ዓመቱ አለቀና የጥምቀት በዓል የሚከበርበት ዕለት ደረሰ እንደተለመደው ወጣቱ በዓሉን ለማክበር ሄዶ ሳለ ልጃገረዶች ለባብሰውና ተኳኩለው በዓሉን ለማክበር ሲመጡ ተመልክተና "ያምና ጥምቀት እኔን ገድለሃል የዘንድሮ ጥምቀት ደግሞ ማንን ትገድል ይሆን" አለ ይባላል እዎ የትዳር ጣዕሙ የሚስትና የልጅ ፍቅር ነው ሚስት ባልዋ ውሉ ሲገባ ፊትዋን የምታጠቁርና ውሃ በቀጠነ የምታንጉራጉር ከሆነ የገድያ ገድያ /የሞት ሞት/ ነው፣ እንዲህ እንዳይሆን የምርጫ ጊዜ ማስተዋልና ማጥናት ያስፈልጋል።

በአሁን ጊዜ ግን ተገናኝቶ ለመወያየት፣ ለመተዋወቅና እርስ በርስ ለመቀራረብ አመች የሆነ ይመስለናል ። ወጣቶች በስብሰባ እየተገናኙ ስለ ሀገር ዕድገት፣ ስለ ማኅበራዊ ኑሮ ስለሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት የሚመካከሩባቸው በርከት ያሉ ሕዝባዊያን ማኅበራትና መንፈሳዊያን ድርጅቶች በከተማና በገጠር ተቋቁመዋል ።አሁን ወጣቶች በየስብሰባው እየተገናኙ ስለ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት ስለሀገራቸውና ስለጠቅላላው ርእዮተ ዓለም በመነጋገር ላይ ናቸው ። ታዲያ በዚህ አጋጣሚ ወጣትዋ ስለማኅበራዊ ኑሮ፣ ስለ ቤተ ሰብእ አመሠራረትና ስለ ኅብረተ ሰብእ ዕድገት ያላት አመለካከት እንዴት ነው?

ወጣቱስ ስለ ሰው ልጆች እኩልነት፣ ስለማኅበራዊ ኑሮ ይዘት፣ ስለ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት ምን ያህል ተረድቶአል? ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ ሁለትና ሶስት ልጆችን ወልዶ መፋታት ለማኅበራዊ ኑሮ ጠንቅ ፣ ለኅብረተ ሰብእ ዕድገት ዕንቅፋት፣ ለክርስትና ሕይወት ውድቀት መሆኑን ተረድቶአል ወይ? ይህን የተረዳ ከሆን ጥሩ የትዳር ጓደኛ ሊሆን ይችላልና ሊመረጥ ይገባዋል ።

ወጣትዋም እንዲሁ ስለ ሀገር ነፃነት ስለ ማኅበራዊ ኑሮ አቅዋምና ስለ ወገን ሀልውና የተረዳች ከሆነ፣ የባል ሀልውና የሚስት፣ የሚስትም ሀልውና የባል ሀልውና መሆኑን ልትረዳ ትችላለች ። ይህንንም የተገነዘበች ወጣት መልካም ትዳርን ለመመሥረት ትችላለች ። በዚህ አጋጣሚ የኑሮ ጓደኛን መምረጥና ጥሩ ትዳርን መመሥረት እንደሚቻል ይታመናል ። ከዚህም ጋር "የሽ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ" እንደሚባለው ሁሉ ማንኛውም ነገር የተቃና ሊሆንና ግቡን ሊመታ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲፈጸም ነው ። ስለሆነም በጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ ይጠቅማል "መልካም ሚስት የጸሎት መልስ ናት" ተብሎ ተጽፎአልና።

ራዶ አስረስ



# ነፍሴ ተመከሪ



ከተማሪ ሊባኖስ ገዳሙ

ፈራሽና በስባሽ ረጋፊ ቀሪ
አላቂና ጠፊ ከንቱ ተሰባሪ ፣
በሆነ ሥጋ ላይ ለጊዜው ብትከብሪ ፣
በአርቲፊሻል ጌጦች ብትሽቀረቀሪ ፣
መሆንሽን ገምተሽ ከዚህ የማትቀሪ ፣
በሠራሽው ሥራ ኋላ ከምታፍሪ ፣
ዛሬውን ተጸጸች ነፍሴ ተመከሪ ፣
ይልቅስ አስበሽ ወደፊት መጪውን ፣
ስለእንቺ ነፃነት የተሰቀለውን ፣
በረሃብና በጥም የተፈተነውን ፣
በሚያስደንቅ ግርማ የሚገለጠውን፡
የሰውን ፊት አይቶ የማያዳላውን
ክፉን እንደሥራው የሚበቀለውን ፣
ለመልካም ጽድቁን የሚያቀዳጀውን ፣
በሲኦል ውስጥ ሆነሽ ኋላ ከመባዘን ፣
የጽድቅ መሠረት አርአያ በመሆን
እንድታመሰግኝ ኃያሉ አምላክሽን ፣
በፍጹም ተስፋ አርገሽ የማይታየውን ፣
ታግለሽ ስትኖሪ መከራን በደልን ፣
በፍቅረ ንዋይ በረሀብ መፈተንን ፣
በእርግጥ ታገኝአለሽ የሕይወት ደኅንነትን
የማትጨብጪውን እንደምትጨብጪው ፣
የማታይውንም አርገሽ እንዳየሽው ፣
በተስፋ ካዳነሽ ጌታን ከለመንሽው ፣
ይህን ነው አምላክሽ ከአንቺ ላይ የሚሻው
በማለት ጳውሎስ እንዳስጠነቀቀሽ ፣
እውነት የሆነውን ቃሉን አስቀድመሽ ፣
የዘለዓለም ቤዛ መሆኑን ተረድተሽ
ለሌሎችም ነፍሳት ችቦሽን አብርተሽ
ነፍሴ ተመከሪ ቅጣትን እንዳትወርሽ
መንፈስና ሥጋ የማይጣጣሙ መሆኑን ገምተሽ ፣
የመጪውን እንጂ የጊዜውን ትተሽ
ከዘለዓለም ሞት ደኅንነትን መርጠሽ
ክፋትን ተንኰልን ወዲያ ከአንቺ አርቀሽ ፣
ለእኔ የሚለውን ከአእምሮሽ አውጥተሽ
ለብዙዎች ደኅንነት ሰላም ተመኝተሽ ፣
ልዑል ፈጣሪሽን ክርስቶስን መስለሽ
መንሳት እንድትችይ በክብር ታጅበሽ ፣
ከፀሐይ ብርሃን ሰባት እጅ ደምቀሽ
ነፍሴ ተመከሪ ተጸጸች እባክሽ
የሥጋን ፍላጐት በርትተሽ ተዋግተሽ
ሥራና እምነትን ጥሩር ጋሻ አድርገሽ
ሕጉን ትዕዛዛቱን በደንብ አስተውለሽ ፣
አርአያ በመሆን በግልጽ አስተውለሽ ፣
አርአያ በመሆን በግልጽ አስመስክረሽ ፣
ልክ እንደፊደላት በሰው ፊት ተነበሽ ፣
የጌታሽን ልጆች ልቡና አርከተሽ
ነፍሴ ተመከሪ ተስማሚ ከአምላክሽ
ይኸንን ከአደረግሽ እስከመጨረሻው ፣
በሞት በመከራ እርሱን ከመሰልሽው ፣
አብሮ ያስነሳሻል ነፍሴ ሆይ እመኝው
በምድር ላይ ስትኖሪ ሰላምን አግኝተሽ ፣
ኋላም በደስታ በክብር ታጅበሽ ፣
ለኢየሩሳሌም ባለቤቷ ሆነሽ
የአትክልቷን ፍሬ መዓዛ ተመግበሽ ፣
ከቅዱሳን ጋራ አብረሽ እልል እያልሽ
በደስታ በጸሎት መኖርን ከፈለግሽ
ዛሬ ነገ ሳትይ እውነቱን መዝነሽ
ስንዴውን ከእንክርዳዱ በደንብ ለይተሽ ፣
በተዋሕዶ እምነት አምነሽና ታምነሽ ፣
ጊዜ ሳትሰጪ በንስሐ ታጥበሽ
በሕይወት መዝገብ ውስጥ እንዲገኝ ስምሽ ፣
ነፍሴ ተመከሪ ተመለሽ እባክሽ
በአንድ ተሰብስበን ከየወደቅንበት ፣
ለፍርድ እንቀርብና ከጌታ መንበር ፊት
ደግ በሠራው ሥራ ሲታደል በረከት ፣
ክፉም በክፋቱ የዘራውን ሲያመርት ፣
ከንቱ እንባን ማዝረክረክ ወይም ጥርስ ማፋጨት
ሊያድን ስለማይችል ከሚመጣው ቅጣት
ነፍሴ ተመዝገቢ በመጽሐፈ ሕይወት
ፈራሽና በስባሽ ረጋፊ ቀሪ ፣
አላቂና ጠፊ ከንቱ ተሰባሪ ፣
በሆነ ሥጋ ላይ ለጊዜው ብትከብሪ ፣
መሆንሽን ገምተሽ ከዚህ የማትቀሪ
በሠራሽው ሥራ ኋላ ከምታፍሪ
ዛሬውን ተጸጸች ነፍሴ ተመከሪ

ሊባኖስ ገዳሙ



www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፤ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

### ምሥጢረ ሥጋዌ

**1. እግዚአብሔር ወልድ ማን ነው ? ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ መሆኑን ቀደም ባለው የጽሑፍ ማስረጃ ተመልክተናል ።**

**እግዚአብሔር ወልድ የአብ የባሕርይ ልጅ (ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው) ስለሆነ ወልደ እግዚአብሔር ይባላል (ዕብ 1፡2) ቃሉም ከመሆኑ የተነሣ ቃለ እግዚአብሔር ወይም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ ይጠራል ። ዮሐ. 1፡1-14 (መድኃኒት በመሆኑም ኢየሱስ ይባላል ማቴ. 1፡22) መሢሕ ወይም ንጉሥ ከመሆኑ የተነሣ ክርስቶስ ተብሎ ይጠራል ።**

**እንዲሁም የእኛን ባሕርይ ወርሶ በእኛ የተፈረደውን ፍዳ ራሱ ተቀብሎ ስለ አዳነንና ሁልጊዜ እኛን ተዋሕዶ አንድነቱን ከእኛ ጋር በማድረጉ አማኑኤል ተብሏል ። (ማቴ. 1፡23 ኢሳ 7፡14) የሥጋም የነፍስም ፈጣሪ ገዥ ስለሆነም በተለይም ከግብርናተ ዲያብሎስ ነፃ አውጥቶ ከፍዳ ከመርገም አድኖ ስለሚገዛ ጌታ (እግዚእ) እየተባለ ይጠራል ። ይህንም በመሳሰለ ሁኔታ ከግብሩና ከባሕርዩ ጋር የተስማሙ ስሞችና ቅጽሎች አሉት ። ወልድ ቅድመ ዓለም ከአብ ተወለደ እንጂ አልተፈጠረም ። ስለዚህም 318 ሊቃውንት የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ ''ሲሉ በጸሎተ ሃይማኖት ገልጠውታል ስለዚህም ፍጹም አምላክ መሆኑ ታውቋል ከአባቱም ጋር በመለኮት አንድ ነውና ትክክል ነው ሁሉ በርሱ ሆነ ያለርሱ ግን ምንም ምን የሆነ የለም (ጸሎተ ሃይማኖትተመልከት (ዮሐ.1፡3፡1ኛቆሮ1፡30**

የክርስቶስን አምላክነት የርሱን ብቻ ንጉሥነት ቅዱስ ጳውሎስ ሲመሰክር የዘለዓለም ንጉሥ የማይጠፋ ብርሃን የማይታይ አንድ አምላክ ስለሆነ ለርሱ ክብር ምስጋና ይገባዋል ። ለዘለዓለሙ አሜን'' ብሏል (1ኛ ጢሞ. 1፡16)

እግዚአብሔር ወልድ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከዕውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ ነው ። እርሱ ከሁሉ በፊት የነበረ ቀዳማዊ አምላክ ነው (ራእ22፡13።) በፍጻሜ ወይም በማዕከለ ዘመንም ሰው ሆኖ ሥጋን ተዋሕዶ ለብሶ እግዚአብሔር ወልድ በሚል ስም መገለጡ ተጽፎአል ። ከኃጢአትም በቀር ፍጹም ሰው ሆነ ሰው የሰራውንም ሁሉ ሠራ(2ኛ ቆሮ. 5፡21) ይህም ሁሉ ሲሆን ከባሕር ይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ አልተለየም ። ልዑላዊ መንበሩንም አልለቀቀም ፤ እርሱ ዕውነተኛ አምላክ ሲሆን ሆኖም ሳለ እውነተኛ ሰው ነውና በዚህም ምክንያት እንደሰው በምድር ተመላልሶ ወጣ ወረደ በዚህም ፍጹም ሰውነቱ ታወቀ ሉቃ 2፡52 ከዚህም የተነሣ ስለርሱ የምንማረውና የምናስተምረው ምሥጢረ ሥጋዌ ይባላል ። ትርጉሙም ሰው የመሆንምሥጢር ማለት ነው ። አምላክ ሆኖ ሣለ ሰው ፤ ሰውም ሆኖ ሣለ አምላክ ነው ብሎ መናገር ከባድና ረቂቅ ስለሆነ ምሥጢር ተብሏል ማለት ነው ። ሆኖም ይህን ሁሉ ምሥጢር ለወዳጆቹ ቅዱሳን(ጻድቃን) አበው ገልጦታል ።

አስረጅ አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ «በአምስት ቀን ተኩል ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ሥጋዬን ቆርሼ ፤ ደሜን አፍስሼ አድንሃለሁ'' ብሎ ተስፋ ሰጣቸው ።

አዳምም ይህን ሁሉ ለልጆቹና ለልጅ ልጆቹ ነገረ ፤ ልጆቹም አንዱ ሲቀር ሌላው ሲፈጠር ትንቢት ሲናገሩ ፤ ሱባኤ ሲቆጥሩ ኖሩ ። በዚህም መሠረት 5ሺህ 5 መቶ ዘመን ሲፈጸም አንድ ሰዓት እንኳ ሳያጉድል ወይም ሳያተርፍ አምላክ ሰው ሆኖ በሥጋ ተወለደ ። ጥቂት በጥቂትም አደገ ከኃጢአትም በቀር ሰው የሚሠራውን ሁሉ እየሠራ ኖረ ። በተወለደም በ30 ዓመቱ በዕደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ ተጠመቀ ከጥምቀቱም በኋላ 3 ዓመት ከ3 ወር በምድረ እሥራኤል እየተዘዋወረ ወንጌልን አስተማረ ።

ትምህርቱም ተስፋፍቶ በሁሉም ዘንድ ሲዳረስ የተናገረውን ትንቢት ለመፈጸም ሕማም ለሞት ተላልፎ ተሰጠ (ተሰቀለ ሞተ) በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ገጽ 65-68 ተመልከት ።

ቄ./ መክብብ አጥናው


# ገብርኤል ማን ነው ?

ከገጽ ፫ የዞረ

ይኖሩ ይሆናል ። እርግጥ በእግዚአብሔር ኃይል የማያምኑ ካሉ ተአምራትን ማስተዋል ይቸግራቸዋል ። ምክንያቱም ተአምራት ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደርጉምና ።

መልአኩ ቅ ገብርኤል ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እስካሁን ድረስ የምሥራችን ያበሠረ ''ራእይን የገለጠ በመከራቸውም ጊዜ የደረሰ ለሚያምኑ ብቻ ነው ። ገብርኤል ከተገለጠላቸው ሰዎች አንዱ ዘካርያስ ለመጠራጠር ቢሞክር ዲዳ እንዲሆን አደረገ ። ስለዚህ ገብርኤል ማን ነው ? ብለን ስንጠይቅ በእግዚአብሔር ለሚያምኑ የሚላላክና የሚያገለግል የሰላምና የደስታ መልአክ እንደሆነ ማስተዋል ይኖርብናል ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ





# የኢትዮጵያውያን ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች

ከአለፈው መጽሔት ቁጥር 26 የቀጠለ
''ክፍል 6''

የመዝገብ ቁጥር (ሰጅል ሳዓድ) 188 = ገጽ 211 = = = የኢየሩሳሌም የሕግ አስተዳደር ፍርድ ቤት (መሐከማ ሽርኢየ ከኢየሩሳሌም ቃዲ ከተከበሩ ሸኽ አሊ ፌት ። በአለፈው ታሪክ እንደቆጠርነው ማስረጃ ። የግብፅ ወገኖች ክርስቲያን ገዳም እንዲመረመር ተደረገ በኢየሩሳሌም (የሐበሾች) ጠበቃ አሳሳቢነት ። ይሄውም ገዳም ጥንት በታወቀው ዴር ሡልጣን በተባለው ገዳም የግብፅ ወገኖች የክርስቲያን ቦታ ነው ። ከአሁን በፊትም ለመታደስ እንዲመረመር በተወሰነው መሠረት ሙአሊም ሳሊም የተባለ ነዳቂ ስለ ግብጽ ክርስቲያን ርስቶች ተነጋገረ ጥያቄ መሠረት ። በተጠቀሰው ጠበቃ አማካይነት ገዳሙ አርጅቶና ፈርሶ ተገኘ ። አንዳንዱ ክፍል ግን አስፈላጊው ጥራሽና መለሰን ሁኖ ተገኝቷል ። ሥራውም መሐንዲሱ ገምቶ በአቀረበው መሠረት ከአሁን በፊት እንደታዘዘው ግምት በመንግሥቱ ቃል እንደ መዘገበው የገዳሙን ዝርዝር በዓይነት በዓይነቱ ለመታደስ አስፈላጊ ሁኖ የተገኘውን ገዳሙንና መተላለፊያውን አፍርሶ ጥንት ከነበረው ሳይጨመር እንዲሠራ አገረ ገዢው ከላይ ለተጠቀሰው ተነጋጋሪ ሙአሊም ሳሊም ለተባለው ለማደስ የሚያስፈልገውን ሁሉ እንዲሠራ አዘዘው ። ነገር ግን ሥራው ከጽሑፉ እንዳይተላለፍ የታዘዘበት ቀን ከላይ እንደተጻፈው ጀማድ አል አውል በተባለው ወር ነው ። ከዚህም ቀጥሎ የተሠራውን በአይነት ለማስረዳት ሙአሊም ሳሊም የተባለው ኃላፊ ወደ ተከበሩ አገረ ገዥ ቀርቦ አስረዳ ። የሥራውም አይነት እንደሚከተለው ነው ። ከላይ እንደተጠቀሰው ዝርዝር ሳይጉድል ሳያንስ ተሠርቷልና ይህ የተጠቀሰው ገዳም እንደገና መሐንዲስ እንዲመረምረው ሲል ጥያቄ አቀረበ ። የኢየሩሳሌም ፓሻ መሐንዲስ ሕባት እላህ የተባለ በአለበት እንደገና ተመረመረና በማዘዣው ልክ ተሠርቶና ታድሶ ተገኘ ። በሰሜን በኩል ያለው ቅርጽ ግን እንደቀድሞው የአትክልት ቦታ ስለሆነ በማዘዣው መሠረት እንደዚሁ እንደጥንቱ ተገኘ ። ደረጃውም እንደ ጥንቱ ተስተካክሎ ተገኘ ከፎቆቹ በታች የሚገኙ ቤቶችም ከነመስኮቶቹ ጭማሪ ሳይኖራቸው ታድሰው ተገኙ ። ደግሞ በስተምዕራብ ያሉ በላያቸው ፎቅ ያለባቸው ቤቶች እንደዚሁ ጭማሪ አልባ ተሠርተው ተገኙ ደግሞ ወደ ጎልጎታ በር መግቢያ የሚያደርሰው ደረጃ መተላለፊያ በር ተገኘ ። ይህም ቦታ የሚጸልዩበትና የሚቀድሱበት ነውና እንደዚሁ እኩል ጥንት እንደተሠራ እኩልም አዲስ ተሠርቶ ተገኘ ። ደግሞ አራቱ ቤቶች በላያቸውም ላይ ፎቅ አምስት ቤቶች ያሏቸው ጭማሪ አልባ እንደ ጥንቱ ታድሰው ተገኙ ። ደናም ወደ ምሥራቅ በኩል የሚገኘው ቅጽር ይሄውም ከፈራረሰው ቦታ ላይ ነው ። ስፋቱም እስከ ሱቁ ድረስ የተያያዘነውና ጭማሪ ሳይኖረው እንደታዘዘው 'ውስጡና ዳሩ ታድሶ ተገኘ ። ደግሞ በስተሰሜን በኩል የሚገኘው ቅጽር ገዳሙን ከሁለት የከፈለው መንገድና መተላለፊያ እንዲሁ ታድሶ ተገኘ ደግሞ ወደ ላይኛው የገዳሙ ቤት የሚያደርሰው መተላለፊያ ጣራውና ግድግዳው እንዲሁ ታድሶ ተገኘ በዚሁም አልፎ በስተምሥራቅ የሚገኙ አራት ቤቶች ከፍ ያሉ ፎቆች ያሏቸው ደግሞም በምድር ቤት የሚገኙ ትልቅ ሳሎንና ትንንሾቹም ቤቶች እንዲሁ በውስጥና በዳር ታድሰው ተገኙ ። ደግሞ እንደዚሁ በስተምስራቅ በኩል ያሉ ትናንሾች ቤቶች ደጃፎቸው ወደ ምዕራብ የሆኑ ታድሰው ተገኙ ደግሞ በስተሰሜን በኩል ከምድር ቤት የሚገኘው አዳራሽ በላዩ ከገጠመው ባልከን ጋር ከእርሱም ጋር ሁለት ቤቶች ላሉበት ተብሎ የተነገረውና በላዩም ሳሎን ያለበት ደግሞ በዚሁ በስተሰሜን በኩል ከገቡ በኋላ የሚገኙት ሰቀላዎች በስተምሥራቅ በስተሰሜንም በኩል ይህ ሁሉ ታድሶና ተሠርቶ ተገኘ ። ደግሞ በማእዘኑ ላይ የፈረሰው ቤት በዚሁም በር እንዲወጣ ተብሎ ትእዛዝ የተሰጠበት የጥንቱ ስለፈረሰ በውስጡና በዳሩ ታድሶ ተገኘ ። ደግሞ ሶርያዎች ያሉበት ቤት በውስጡና በዳሩ ታድሶ ተገኘ ሲላህ የተባለ የተቀመጠበትም ቤት እንዲሁ ተሠርቶ ተገኘ ። በስተደቡብ ያለውም አዳራሽና በስተምዕራብ ከሚገኙ አራት ቤቶች ጋር እንዲሁ ታድሰው ተገኙ ደግሞ ከማዕዘናቱ በታች የሚገኘው ቅጽር ማዘዣው እንደሚዘረዝረውና ጥንት እንደነበረው ይሁን ተብሎ የታዘዘው በደቡብ በኩል ተሠርቶ የነበረው አሁን ወደምሥራቅ አሳለፉት በምዕራብና በጉንም የተያያዘ ነው ። ደግሞም አራተኛው በር መተላለፊያ መዘዋወርያ ተብሎ የተሰየመው ይህ ሁሉ ታድሷል ። በዚህም አጠገብ ያሉ ቤቶችና ምድር ቤቶች እንደዚሁም መካከለኞች ናቸው። እንደዚሁም ታድሰዋል የገዳሙ አስፈላጊ ሁሉ ከላይ እንደታዘዘው ሳይጨመር ተሠርቷል ተብሎ ተመስክሯል ። መጀመሪያ ለምርመራ አስፈላጊ ነው ተብሎ በቀረበው መሠረት ምንም ሳይጉድል ተሠርቶ ተፈጽሟል ። ለመሠራቱ የተጻፈው ትክክለኛው ቃል በሕጉ መሠረት ተመዝግቦ ሸዋል በተባለው ወር 13 ቀን 1098 ዓመተ ሕጅራ ተጻፈ ።

ይህ ከዚህ በላይ የሰማነው ከዋናው የርስት ክፍል መዝገብ የተገኘ ነው ። ስለ ትክክለኛው ግልባጭ የተከፈለ ተንቤር የ150 ማንቲም ራቢእ አል አወል በተባለው ወር በ1371 ዓመተ ሕጅራ 6/12/1951 ዓ.ም. (ፈረንጅ) ፊርማ የመዝገብ ቤት ጠቅላይ ሹም ውስፊ አል ባይዲ ደግሞ የዋናው ዳኛ የኢየሩሳሌም ቃዲ ሸክሑልሚ አል ሙሕተሰብ ማኅተም የሕግ አስተዳደር ፍርድ ቤት ይህ ትክክለኛ ግልባጭ የተጻፈው ከልዩ መዝገብ ቤት ነው ። የመዝገቡም ቁጥር 188 ገጽ 211 የተገኘ ነው ። ለዚሁ የገንብ የተከፈለበት አንድ ፓውንድ ነው ። ለዚሁም የደረሰኙ ቁጥር 494721 ነው የተከፈለበት ቀን 6 12 1951 ዓ.ም. ፊርማ ውስፊ ባይዲ ማኅተም (መሐከማ ሽርኢየ አል ቁድስ) የኢየሩሳሌም የሕግ አስተዳደር ፍርድ ቤት ።

ማሳሰቢያ ደግሞ ወደ ጎልጎታ በር መግቢያ የሚያደርሰው ደረጃ ያለው መተላለፊያ ከሚለው ላይና ደግሞም የሡልጣን ሳሊም ፊርማ ጽሑፍ ላይ እንደዚሁ በጎልጎታ ጥግ በስተደቡብ በኩል በምድር ቤት የሚገኘው የሐበሻ ቤተ ክርስቲያን በሩም ወደ ደቡብ የሆነና ትልቁ ገዳም ዴር ሡልጣን የዚሁም መንገድ በር በጎልጎታ ደጃፍ አደባባይ የሆነ ከሚለው ላይ መሰሉን ሳይለውጥ መናገሩን ጠንቅቀህ ተመልከት ደግሞም የአራተኛው ሡልጣን መሐመድ ፊርማ ላይ ስለ ሐበሾች ርስት ለግሪክ ሊቀ ጳጳሳት ከሰጠው ትእዛዝ የመዝገብ ቁጥር 151 ገጽ 9 ላይ ከሚገኘው ስንመለከት ከጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን የተያያዘ በስተ ደቡብ በኩል ብሎ የኢትዮጵያ ገዳም ተረክቦ ይህም ገዳም በጎልጎታ በር አደባባይ ነው መንገዱ ብሎ የሚዘረዝረውን ተመልከት የገዳሙ ስፋት የተጠቀሰው ፊርማ 211 ገጽ ላይ የሚገኘው አስረድቶናል ። ይህም ፊርማ የግብጽ ወገኖች ክርስቲያኖች ገዳም ጥንት የታወቀ በዴር ሡልጣን በማለቱና እኛም የግብፅ ክርስቲያን መባል ስግችን መሆኑን እንድትረዱት ግብጾችን ግብፅ ይላቸዋል እንጂ የግብፅ ወገን ክርስቲያንን አይላቸውም ።

ይህ ቀዋሚ የሆነ ማስረጃችን ከርስት ክፍል በመንግሥት መዝገብ የተመዘገበ ከመሆኑም በላይ 1ኛ/ ቻሩሊ ከተባለ ከ2ኛ መጽሐፍ ከገጽ 171 እስከ ገጽ 173 ድረስ ተጽፏል ። 2ኛ/ ግብጾች የርስት መዝገብ ብለው ከጻፉት የእነሱ አቡነ ማቴዎስ ፊርማ የሚገኝበት የሽፍጥ መጽሐፋቸው ከገጽ 80 እስከ 81 ድረስ ሦስተኛ ማስረጃችን ብለው መዝግበውታል ዋና የሚጠቀሙበት ቃልም የግብፅ ወገን ክርስቲያን ገዳም የምትለውን ቃል አገኘን ብለው ነው ። ይህንንም ማስረጃ የእኛ ብቻ መሆኑን በዴር ሡልጣን ገዳም ጥንት የታወቀ በሚለው ቃል በ1943 ዓ.ም. የኤሽናፊንቱ አቅጣጫ ወደኛ ነበር ግን ምን ይሆናል ምክንያቱ በጊዜው ያስረዳሁት ይበቃል ። አሁንም ማስረጃውን በትክክል አውቃችሁ ሥሩበት መብቱ የጠቅላላ ኢትዮጵያውያን መብት ነው ።

መምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት



www.ethiopianorthodox.org

# የወጣቶች ዓምድ

## ወጣቶች እራሳቸውን በንጽሕና እንዴት መጠበቅ ይችላሉ ?

ከኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

(ካለፈው የቀጠለ)

ዝሙት ኃጢአት መሆኑን ባለመገንዘባቸው "የሥጋ ፍላጐት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስለሆነ መርካት ያለበት የተፈጥሮ ሕግ ነው" እያሉ ያለምንም ሥጋት የዝሙትን ተግባር የሚፈጽሙ አንዳንድ ወጣቶች እንዳሉና በተለይም አንዳንዶቹ ከእጮኛቸው ጋር የሚፈጽሙት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሐጢአት ነው ብለው ስለማያስቡ ያለ ምንም መሰቀቅ እንደሚፈጽሙት ባለፈው ዝግጅታችን ጠቅሰን ሰፋ ያለ ማብራሪያ መስጠታችን የሚታወስ ነው ። የአሁኑም ዝግጅታችን የዚያው ተከታይ ይሆናል ።

በመሠረቱ ባለፈው ጊዜ የተመለከትነው ሳይጋቡ የሚፋቱት እጮኛሞች ምን ዓይነት ችግር እንደሚያጋጥማቸው ነበር ሆኖም ሁለትእጮኛሞች አስቀድመው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከተዋወቁና በዝሙት ከወደቁ በኋላ ምንአልባት ተሳክቶላቸው የጋብቻቸውን ሥነ ሥርዓት ለመፈጸም ቢበቁስ? የሚል ጥያቄ ይቀርብ ይሆናል ። በርግጥ ኋርሱም ሆነ እሷ ቃላቸውን አክብረው ወደ እውነተኛው ጋብቻ ከደረሱ ምን አለበት? የሚሉም ሊኖሩ ይችላሉ ። የብዙዎቹ አስተያአየት ግን በመጀመሪያ የዝሙት ጠባያቸውን በማርካት ፍቅራቸውን ከጨረሱ በኋላ የሚጋቡ እጮኛሞች አብሮ የመኖር እድላቸው የመነመነ ሊሆን ይችላል የሚል ነው ። ለምን ? ቢባል በመካከላቸው ያለው መተማመን ተወግዶ ጥርጥር እየተስፋፋ ይሄድና ልጅቱ ምናልባት እኔን በቃላት እየደለለ እንዳባለገኝ አሁንም ከሌላይቱ ጋር እንደዚሁ ያደርግ ይሆናል" እያለች በማሰብ ባሏ ወደውጭ ወጥቶ ባመሸ ቁጥር በቅንዓት እየተቃጠለች ሥራዋ ንዝንዝና ንትርክ ይሆናል ወንዱም እንደዚሁ ነው በዚህ ሳቢያ ፍቅራቸው እየተጎጠጠ ይሄድና አብሮ የመኖሩ ጉዳይ ወደ ማከተሙ ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል እንዳጋጣሚ የእህል ውኃ ጉዳይ ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ አብረው ቢኖሩም ኑሮዋቸው ለዛ የሌለው አተላ ይሆናል ። ይህም የሚሆነው ከጋብቻ በፊት የዝሙትን ሥራ የሚፈጽሙት ወጣቶች አስቀድመው ፍቅራቸውን ስለሚጨርሱና ስለሚጣገቡ ወደፊትም የሚጠብቁት አዲስ ነገር ስለማይኖራቸው ነው ።

ከጋብቻ በፊት ዝሙትን የሚለማመዱ ወጣቶች ነውራቸውን ለመሸፈን ብዙ ጥረት ስለሚያደርጉ በጠባያቸው የተበላሹና ተስፋ የቆረጡ ይሆናሉ ። በራሳቸውም መተማመን ስለሚያጡ ከቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓትና ከእምነት ክልል ውጭ በመሆን ራሳቸውን ለማግለል ይሞክራሉ። ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔርን ስም መስደብ ይጀምራሉ ይህም ኃጢአታቸውን ባስታወሱ ቁጥር የመዳን ተስፋቸው የመነመነ መስሎ ስለሚታያቸውና በዚህ ምክንያት ልባቸው እየተሸበረ እግዚአብሔርን ከካዱ ከፍርድ ነፃ የሚሆኑ እየመሰላቸው ነው ። ግን ይህ አስተሳሰብ ግብዝነትና በጣምም ሞኝ ነት ነው ።

ያም ሆነ ይህ ሴቶችና ወንዶች ጓደኞች ቢሆኑ ይከፋል ወይም ኃጢአት ነው ለማለት አይደለም ፣ መጋባትም ኃጢአት አለመሆኑ የታመነ ነው ዓመፅ የሚሆነው ግን ከጋብቻ ውጭ የሚደረገው ሕገ ወጥ ግንኙነትና ከንቱ የሆነ ርኩስ ምኞት ነው። ታዲያ እንዲህ ከሆነ በእሳት ባኅርይ ያሉ ወጣቶች ይህን የዝሙት ፈተና መቋቋምና ማሸነፍ እንዴት ይችላሉ ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እጅግ ሊያዳግትም ይችላል ቢሆንም ተፈጥሮን እንኳ በቁጥጥር ሥር አድርጋለሁ እያለ በመጣጣር ላይ የሚገኘ የሰው ልጅ ራሱን መቆጣጠር አይችልም ማለት በጣም ደካማነት ይመስላል ስለዚህ ራስን በትእግሥት እየገሩ ስሜትን መቆጣጠር ነው ። ይህም ካልተቻለ ራስን ለኃጢአት ከማጋለጥ ይልቅ ከፈተናው ለማምለጥ መሞከር ጠቃሚ ስለሆነ ከዝሙት መሸሽ ፈሪነት ነው ለማለት አይቻልም ለምሳሌ ዮሴፍ የጲጥፋራ ሚስት በዝሙት ልታጠምደው ባሰበች ጊዜ ልብሱን ጥሎ በመሸሹ ራሱን የመግዛትና የጨዋነት ምሳሌ ሆነ እንጂ የፍርሃት ምሳሌ ነው ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍም በታሪክም አልተወቀሰም ። ስለዚህ የወጣትነትን ዘመን በንጽሕና አሳልፎ ወደተቀደሰ ጋብቻ ለመድረስ የሚከተሉትን ዘዴዎች መከተል ይበጃል የሚል አስተያየት አለን ።

1 - ወጣቶች በጓደኝነት ደረጃ መተዋወቃቸው ጥሩ ሲሆን ለጓደኝነትና ለጨዋታ የሚገናኙበት ሥፍራ ሰዎች ያሉበትና ገላጣ ካልሆነ "እሳትና ጭድ በአንድ ምድጃ" እንዲሉ ሥጋዊ ጦር ሊቀሰቀስባቸውና በፈተናም ላይ ሊወድቁ ስለሚችሉ በተቻለ መጠን ብቻቸውን በሠዋራ ሥፍራ ረዘም ላለ ጊዜ ባይገኙ መልካም ነው እንላለን ።

2 - ክፉ አሳብ መጥፎ አድራጎትን ስለሚያስከትል አስተሳሰብንና ንግግርን መቆጣጠር አስፈላጊ ነው ። " ሰው በልቡ ሞልቶ ከተረፈው ይናገራል" ተብሎ እንደተጻፈ ማንኛውም ሰው በልቡ ያሰበውን ይናገራልና ስለዝሙት በማውራትና ሌሎችም ስለዚሁ ጉዳይ ሲያወሩ በመስማት ነገሩንም አብሮ በማዳመቅ ራሳችንን ለፈተና እያጋለጥን በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ እንዳንገባ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

3 - ፍትወተ ሥጋን የሚቀሰቅሱ መጻሕፍትን ከማንበብና የሞራል ውድቀትን የሚያመጡ የምዕራባውያን ፊልሞችና ፎቶግራፎችን ከመመልከት በየመጠጥ ቤቱም እየዞሩ በአልኮል አንጎልን ከማደንዝ ጠቃሚ መጻሕፍትን በማንበብ ልዩ ልዩ የተግባረ ዕድ ሥራዎችን በመሥራት የሙዚቃ መሣሪያዎችን በመለማመድና መዝሙር በመዘመር ፣ ጂምናስቲክ በመሥራት፣ ልዩ ልዩ ቦታዎችን በመጎብኘት ፣ በመንፈሳውያን የወጣቶች ማኅበራት እየተገኙ በመማርና በማስተማር ሌላም መንፈሳዊ ተግባርን በመፈጸም የእረፍት ጊዜን ማሳለፍ የእውነተኞች ክርስቲያኖች ተግባር በመሆኑ በዚህ ዓይነቱ ተግባር በመጠቀምና መንፈሳዊ ዝንባሌያችንን በማጠናከር ራሳችንንም ከክፉ ሥራ ሁሉ አግልለን ስሜታችንን በመቆጣጠር ከዝሙት ወጥመድ ለማምለጥ እንችላለን ።



# የአራት ቀን ሰሚናር በባሕር ዳር

በደብረ ማርቆስ ፣ በጐንደርና በባህር ዳር መንፈሳውያን ማኅበራት ሕብረት የተቋቋመው የአሥራት አስተዋጽኦ ማኅበር ፣ ከጥቅምት 1 - 4 በባህር ዳር ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤ/ክርስቲያን መንፈሳዊ ሴሚናር አካሄደ ፡-

ይህ ማኅበር በሦስቱ ማህበራት ተቋቁሞ ሥራውንከጀመረ አንድ አመት አልፎታል ። የማኅበሩ አባላትም ከሁለት መቶ በላይ ናቸው ። ከነዚህም ውስጥ አብዛኞዎቹ የዘላለም አምላክ እግዚአብሔር ሰው ሁሉ አሥራትን እንዲያወጣ ያዘዘውን ትዕዛዝ ከልብ ተቀብለው አሥራትን የሚያወጡ ሲሆን የቀሩት በከፍተኛ ትምህርት የሚገኙና በሥራ ሲሰማሩ አሥራትን ሊያወጡ የወሰኑ ናቸው ።



የሰሚናሩ ተካፋዮችና መምህራን

### የማኅበሩ አላማ

#### 1ኛ/ ስለቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት

በአሁኑ ጊዜ እንደሚታወቀው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚገባቸው አልተያዙም ፣ ያላቸውንም እውቀት ለተተኪ ትውልድ እንዲያስተላልፉ አልተደረገም ፣ ስለዚህ ሊቃውንት ከሆሉበት ተፈልገው በቂ ደመወዝ እየተከፈላቸው እውቀታቸውን ለትውልድ እንዲያስተላልፉ ለማድረግና ደቀመዝሙሮቻቸውም እንደድሮው ሰፊ ጊዜያቸውን በዕለት ምግብ ፍለጋ የሚጨርሱ ሳይሆን የተወሰነ ደመወዝ እየተሰጣቸው እንዲማሩ ለማድረግ ነው ።

#### 2ኛ/ ስለሰባክያነ ወንጌል

የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ ለሕዝብ ወንጌልን ማስተማር ስለሆነ ፣ ለምእመናንም ሆነ ለወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት እየተዘዋወሩ ወንጌልን የሚያስተምሩ መምህራንን ለመቅጠር ነው ።

#### 3ኛ/ ስለቅርሳቅርስ

ቤተ ክርስቲያናችንን በውጭም ሆነ በውስጥ ሀገር ታሪኳን የሚያሳውቁ ጥንታውያን ቅርሳቅርሶችን በሚገባ ለመንከባከብ ነው ።

ለምሳሌ ፡- ምትክ እያጡ ያሉት በውጭም ሆነ በውስጥ ሃገር የተደነቁ የትርጓሜ መጻሕፍትን ማሳተም ።

ይህ ማኅበር ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በሥራ ለመተርጐም እንዲቻል አባሎቹን በአመት አንድ ጊዜ በመሰብሰብ እንዲወያዩና ከሊቃውንት አባቶቻችን ትምህርት እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ስለሆነም ለመጀመሪያ ጊዜ ከጥቅምት 1 - 4 አባሎቹን ከእየአሉበት ጥሪ አድርጎ መንፈሳዊ ሰሚናር አካሂዶአል ሴሚናሩንም የጐጃም ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በጸሎት ከከፈቱ በኋላ የአውራጃው አስተዳዳሪ የሺአለቃ ኃይሌ መለሰ አጭር ንግግር አድርገዋል በንግግራቸው ውስጥ" ... ዛሬ ያለው ሕዝብ ካለበት የታሪክ ደረጃ የደረሰው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጠባቂነት ነው ። ከዚህም ጋር እንቢ ለጠላት አልንበረከክም በማለት እነ አቡነ ጴጥሮስ ለሀገር ነፃነት ሕይወታቸውን ሠውተዋል" በማለት ንግግራቸውን ሲያጠቃልሉ ሴሚናሩ ጥሩ ውጤት እንዲያስገኝ ያላቸውን ምኞት ገልጠዋል ። በተካሄደው ሴሚናር ከሊቃውንት ጉባኤ አለቃ አያሌው ታምሩ (የሊቃውንት ጉባኤ ሊቀመንበር) ፣ ከወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ዲያቆን ለይኩን ብርሃኑ የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ ከሐዋርያዊ ድርጅት መሪ ጌታ ሰይፈ ሥላሴ የትንሣኤ መጽሐት አዘጋጅ በተለያየ ርእስ ትምህርት ሰጥተዋል ከጐጃም ሀገረ ስብከትም መ ያዕቆብ ጌታሁን የጐጃም ሀ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ፣ ከባህርዳር አውራጃ ቤ ክህነት መምህር ገ ሥላሴ ካሣ የአውራጃው ቤ ክ ሥራ አስኪያጅ ተገኝተዋል ።

በአንድ አንድ ችግር ጥቂቶች ቢቀሩም የማኅበሩ አባላት በብዛት ተገኝተዋል ። ይህ የአሥራት አስተዋጽኦ ማኅበር ሴሚናር እንደሚካሄድ የሰሙ አንድ አንድ ሰዎች ከልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገራት ተገኝተዋል ።በባሕር ዳር አካባቢ ከሚገኙ ገዳማትም ጥሪ የተደረገላቸው አባቶች ተገኝተዋል ።

በሴሚናሩ በተለያዩ መምህራን የወንጌል ትምህርት ተሰጥቶአል ፣ ልዩ ልዩ መንፈሳዊና ታሪካዊ ሥነ ጽሑፎችም ተነበዋል ። በየቀኑ በፕሮግራሙ ጣልቃ በምርጥ መዘምራን የሰሚን አእምሮ የሚማርኩ ልዩ ልዩ መዝሙሮች ተዘምረዋል ። በልዩ ልዩ የቤ ክርስቲያን ችግሮች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጐአል የማኅበሩ አባላትም ማኅበሩን በማዕከላዊነት የሚመሩ ሰባት ሰዎችን መርጠዋል ። ለወደፊትም ማኅበሩ ሀገር አቀፍ የሚሆንበትን ሁኔታ በሴሚናሩ ውይ


ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቁጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ


ለትንሣኤ መጽሔት ምን እህርዳዎ ዓምድ አዘጋጅ፣
አዲስ አበባ

ከተጋባን 5 ዓመታችን ነው በዚህ የጋብቻ ጊዜ አችን ውስጥ ሶስት ልጆች ወልደናል ። ከባለቤቴ ጋር ተዋውቀን የተጋባነው ቡና ቤት ውስጥ ነው በፊት ሰካራም መሆኑን ባውቅም በአሁኑ ጉዜ ስካሩ ብሶበታል ፣ ከሶስት ጊዜ በላይ በሰዓት እላፊ ተይዞ የተቀጣ ቢሆንም በሰዓት እላፊ እየተያዘ ቀበሌ ያደረበትን ቀን ቆጥሬ አልዘልቀውም ።

ሰው ከተኛ በኋላ እየገባ በሚያነሳው ረብሻ የልጆቻችን ሕይወት ከእሰቃቂ አደጋ የዳነ ቢሆንም ጐረቤቶቻችን በእኛ ጩኸት ሰልችተዋል ።

በየጊዜው እኔን ካልገደልኩ እያለ ከገላጋይ አልፎ የቀበሌ ሕዝብ ደህንነት አባላት እየተጠሩ ነው ሕይወቴ የሚተርፈው ።

ስለዚህ ምን ማድረግ ይሻለኛል ? ቢሰማህ እባክህ በዓምድህ ምክርህን አስተላልፍልኝ ።

ስሜን ደብቅልኝ
ከአዲስ አበባ

ስካር ሕይወትን የሚያሳጣ ፣ በጀብደኝነት ወንጀል የሚያሰራ ፣ በመጨረሻም የራስን ሕይወት የሚያሳጣ የትዳር ነቀርሣ ፣ ቤተሰብን በመልኩ ለማሳደግ የማያስችል የሰዎች ጠላት ነው ።

ስካር ያጨቃጭቃል ፤ ከዚህም አልፎ በሕይወትና በንብረት ላይ ጉዳት ያደርሳል ። በዚህም ምክንያት ብዙ ትዳሮች በእንጭጫቸው ተቀጭተው ፈርሰዋል ።

ብዙ አዳጊ ሕፃናትም ማንዘራሽ ሆነው የሀገራችን ሸክም ሆነው ዛሬ መንግሥት ካለበት እጣዳፊ ችግር ጋር አሳዳጊ ያጡ ሕፃናት ፣ ችግርም ተጨማሪ በመሆን በአሁኑ ጊዜ ለአዳጊ ሕፃናት መንግሥት ማንኛውንም አስፈላጊ ዕርዳታ እያደረገ ነው ።

የእርስዎም ባለቤት እንዲህ ዓይነት ችግር ካለባቸው በእውነቱ ከዚህ መጥፎ ነገር እንዲወገዱ እርስዎ ማንኛውንም ጥረት ማድረግ አለብዎ ።

ታዲያ ከዚህ ነገር ባለቤትዎ እንዲወገዱ ለማድረግ የሚችሉት በማበሳጨትና ጥዋት ማታ በመጨቅጨቅ ሳይሆን በፍቅር ፤ በትህትና ፤ በትዕግሥት መሆን አለበት ።

በቅርቡ ስለቤተሰብና የጋብቻ አማካሪዎች ኮርስ በማድረግ ከሱራሊዮን የተመለሱትን ወ/ሮ ብርሃን ተድላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ባልደረባ ስለዚሁ ጉዳይ ጠይቀናቸው የሚከተለውን ምክራዊ መልስ ሰጥተውናል ።

ጠያቂዋ የጠየቁት ጥያቄ በእውነት በሀገራችን በብዙ ቤተሰቦች ውስጥ የተለመደና የሚደረግ ስለሆነ ያሳዝናል ። ብዙ ቤተሰቦችም በእንደዚህ ያለ ችግር እንደተዋጡ የብዙም ቤተሰብ ትዳር በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ እንደፈረሰ አይተናል ።

የፈረሰ ጋብቻም የጎዘን ጠንቅ መሆኑን ማንም ሰው ያውቃል ። እረ ለመሆኑ ስንቶች ናቸው ያለ አባት ወይም ያለ እናት ፍቅር የቀሩ ? ይህም ከወላጆች አንዳቸው ስለሞቱባቸው ብቻ ሳይሆን በመጣላት ስለተፋቱ ጭምር መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው ። ከዚህም ሌላ ከፍቾው ባይደርሱም በብዙ ሥፍራ እንደሚታየው ወላጆች ለልጆቻቸው መጥፎ አርአያ በመሆን ሕገ ወጥ ተግባር ሲፈጽሙ መታየታቸው ያሳዝናል ። ለምሳሌ አባት ለቤተሰቡ የወር ቀለብ መሸመቻ ገንዘብ በመስጠት ፋንታ የወር ደመወዙን ተቀብሎ በየመሸታ ቤቱ ያባክነዋል ሚስትም በበኩሏ የግል ፍላጐቷን በመፈጸም ቤቷንና ልጆቿን አታስባቸውም ልጆችም ከፍ ሲሉ በበኩላቸው የአባትና የእናትን አርአያ በመከተል የሚቆጣጠራቸውም ከማጣት እንደ ወላጆቻቸው ይፈጽማሉ ስለዚህም የወላጆችን የስካር አመል እንደ ቅርስ ወርሰው ሲሰቃዩ ማየቱ በጣም ያስቅቃል ።

በጠቅላላው የሰካራም ቤት የቻለው ችግር ጭቅጭቅ መንገላታትና ሥቃይ ተዘርዝሮ አያልቅም ቢባል ማጋነን አይሆንም ። ይሁንና ጠጭዎች በተለይም ወንዶች መጠጥ ቤት በመሄድ የሚሠክሩበት ምክንያት የተለያየ እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ ። በተለይ ያላገቡ ወንዶች ከማግባታቸው በፊት መጠጥ ቤት ሄደን እየጠጣን የምናመሽው ከቤት ገብተን ብቻችንን ማምሸት ስለሚያስጠላን ጊዜ እንዲያልፍልን ስንል ነው እንጂ ከአገባን በኋላ ግን በፍጹም እንጠጣም መጠጥ ቤትም አናመሽም በማለት ሲምሉና ሲገዘቱ ይሰማሉ ።

ባለትዳር ወንዶች ደግሞ ሚስቶቻችን ስንገባና ስንወጣ በንዝንዝ ስለሚያበሳጩንና እቤት ሰላም ስላጣን ብስጭቱን እንድንረሳው ስንል ነው [illegible] ሲሉ ሌሎች ደግሞ ባይገርማችሁ በቤታቸው ውስጥ ሰላም ያላቸው ባለትዳር ወንዶች እመጠጥ ቤት ያለው ቻቻታና ውካታ ስለሚያስደስታቸው ብቻ መጠጥ ቤት ያመሻሉ ። እንግዲህ መነሻው ይህንንና ይህንን የመሳሰለ መሆኑን ባጭሩ ካወቅን ዘንድ ወደ ጠያቂዋ ፍሬ ነገር መለስ እንበልና እንመልከት ጠያቂዋ ሲጠይቁ ከባለቤታቸው ጋር በመጀመሪያ የተገናኙት በቡና ቤት መሆኑንና ቀድሞም ቢሆን ጠጭ መሆናቸሆን ገልጸው ቢሆንም አሁን እንደባሰባቸው ጠቁመዋል ። እንግዲህ እንደ እኔ አስተያየት ባለቤትዎ እርስዎን ከማግባታቸው በፊት ወንደላጤ ከነበሩ ጠጪ ሊሆኑ የቻሉበት ምክንያት ከላይ እንደገለጽኩት ብቸኝነቱ ስለሚሰማቸውና ደስታ በመጠጥ ይገኝ ይመስል ለማንብየ ነው ልጅ የለኝ ሚስት ለአንድ ራሴ ለምን አልደሰትም? በማለት ሊሆን ይችል ይሆናል ። የእርስዎም አስተሳሰብ ስንጋባ ይህንን ጠባዩን ይተዋል ብለው በተስፋ ተጋብታችሁ ይሆናል ወይም ባጋጣሚ በመውለድም ሊሆን ይችላል አሁን ባሰበት ስላሉት መቸም መጠጥ መጀመሪያ ሲገባ እየጣፈጠ ይገባና ከጊዜ ብዛት እየተለማመዱት ሲሄዱ እየቀጠለ ይሄድና ደንበኛው ያደርጋል ። በሌላ በኩል ደግሞ እርስዎ ከመጋባታችሁ በፊት ያሳዩአቸው የነበረውን ጠባይ ተጋብተናል በእጄ አድርጌዋለሁ ብለውና ቀድሞውንም ከመጠጥ ቤት ከሌሎች ሴቶች ጋር ሲዳሩ እንደሚያዩት በዚሁ ምክንያት እየቀኑ ሲገቡና ሲወጡ የት አመሸህ ከማን ጋር ሄድክ የትዋልክ ምን በላህ እያሉ ጭቅጭቅ አብዝተውባቸው ከሆነ መጠጣቸውን እንደ መተንስ ለብስጭት ማስረሻ ጊዜ ማሳለፊያ እየጨመሩበት ሄደውም ይሆናል ።

ለምሳሌ እምሽተው ሲመጡ ምክንያታቸውን ከመስማትዎ በፊት ፊትዎን አጥቁረው እየተነጫነጩ ቢነዘንዟቸው ወይም በመካከላችሁ መተማመን ከሌለ ፤ በሃሳብ ፤ በሃይማኖት የማትግባቡ ከሆንና የመነሳሉትንም አለመግባባት በመካከላችሁ ካለእንኳን መጀመሪያውኑ ጠጭ የነበረ ሰው ጠጥቶ የማያውቀው ጠጪ ሊሆን ይችላል ።

በሌላ መንገድ ደግሞ ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ አምሳል እንደመሆናቸው መጠን በቤታቸው ውስጥ ሰላም ካለ አንዳንድ ጊዜ በመካከል ጎደኛ ወይም ወዳጅ መስሎ በሁለቱ መካከል ሰላም እንዳይኖር ለባልዩው አንድ ወሬ ሲነገረው ለሚስቲቱ ደግሞ የተለየ ወሬ በመናገር ቤታቸው እንዲፈርስ በመካከላቸው ሰላም እንዳይኖር የሚያደርግ ወዳጅ መስሎ ጠላት ስለሚኖር በዚህም በኩል መመርመር አይከፋም ከሁሉም ይበልጥ ግን በትዳር መሃከል የእርስ በርስ መተማመንና ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲኖር ያስፈልጋል ።

ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ "አንድ ወንድ ላንዲት ሴት" እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም" "ሰው አባትና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር አንድ ይሆናል"በሚሉት በነዚህ ሦስት ዓይነተኛ ጉዳዮች ምክንያት ባልና ሚስት በመካከላቸው እንከን እንዳይኖርባቸው ተጠንቅቀው ተጋብተው ተስምምተውና ተሳስበው ይኖሩ ዘንድ የላፊነት እንዳለባቸው ማወቅ ይኖርባችኋል ። ሕይወታችሁንም ለእግዚአብሔር ማስረከብና በእርሱ ማመን አለባችሁ ሕይወቱንም ለእግዚአብሔር የማያስገዛ ሰው መልካምን አያይም ። ስለዚህ መልካምን ለማየትና ሰላምን ለማግኘት ትእዛዛቱን መጠበቅ ፍቱን መድኃኒት ነው ።

እንግዲህ ባለቤትዎ የመጽሔታችን ተከታታይ ከሆኑ በበኩሌ የምሰጣቸው አስተያየት በመጀመሪያ ምንም እንኳን የጠጭነት ልምድ መነሻው የተለያየ ቢሆንም እብዛኛውን ጊዜ ባለትዳር ወንዶች በብስጭት መነሻ ጠጭዎች እንደሚሆኑ ከላይ ተነጋግረናል ። በዚህም መነሻ የሚለመድ የአልኮል መጠጥ ሱስ አጣድፎ ከአደጋ ላይ የሚያደርስ መሆኑ እሙን ነው ስለዚህም ሊሆን ይችላል ጠያቂዋ እንዳሉት ፀባችሁና ከርከራችሁ ከራሳችሁ አልፎ ከልጆቻችሁ ከዚያም ከጐረቤት ወደ ቀበሌ የደረሰው ።

ስለዚህ መጠጥ የእእምሮ ጉድለት የአካል ድቀት የነርቦች መወባሰብ የሚያመጣ አደገኛ ሱስ ከዚያም አልፎ ወደ ልጅ የሚተላለፍ በሽታ መሆኑን ተረድተው እንዲተውትና በቤትም ውስጥ የሚበሳጩበት ነገር ካለ ያ ነገር (ስህተት) እንዳይደገም ለማድረግ አስበውና አስተውለው ሳይጠጡ በረጋ መንፈስ በመጀመሪያ ከአእምሮዎ ጋር በመመካከር ልጆቻችሁ በሌሉበት ከፍል በግልጽ ከባለቤትዎ ጋር መወያየትና ጥፋተኛው ጥፋቱን አምኖ ወዲያውኑ ሳይውል ሳያድር ይቅርታ አድርጋችሁ እዚያው እንዳላችሁ ክርስቲያኖች ከሆናችሁ ማለቱ ነው በኅብረት ጸሎት አድርጋችሁ በቤታችሁ ውስጥ የሰላም አምላክ እግዚአብሔር ሰላም እንዲመሠርትላችሁ ብታደርጉ መልካም ይመስለኛል ።

ከዚህም ሌላ የባልና የሚስት ፍቅር ጽኑና በሰው ወሬ የማይፈታ መንፈሳዊ መሆን አለበት ፤ መንፈሳዊ ፍቅር ከፍተኛ ዋጋ ያለው ከሙኑም በላይ የእግዚአብሔር ፍላጐትም ነው ።

ይህ ታላቅ ፍቅርም የቤትን ጽኑ መሠረት የሚጥል መሆኑንና እውነተኛ ፍቅር ራሱ ፈጣሪ ስለሆነ ፍቅር ባለበት ቤት ሁሉ እርሱም በመካከላችሁ እንደሚኖር ማመን አለብዎ ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መጠጥ ሲናገር የወይን ጠጅ ፌዘኛ ያደርጋል በዚህም የሳተ ሁሉ ጠቢብ አይደለም ምሳሌ ም.20 ቁ 1 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ስካር ብዙ ሌሎች ጥቅሶችም አሉ እንግዲህ እርስዎም የጠጭነት ትርፉ በሽታና ከላይ የተዘረዘሩትን መጥፎ ነገሮችን በሰው ዘንድም መጠላትን ያተርፋል እንጂ ሌላ የሚያስገኘው ትርፍ የለም ። በመጠጥ ኃይል የተለከፈ ሰው ለራሱ ዝቅተኝነት የሀገር ሸክም የወገን ሃፍረት መሆኑንም መረዳት አይከፋም።

የመጠጥ ጉዳት ቀስ በቀስ የሚያጠቃ እንጂ በመጀመሪያ የማይታወቅ አደገኛነቱ የላቀመሆኑን አይርሱ ። በደረቅ አንጀትዎ ሲጠጡ ትርፉ ምን ይመስልዎታል ? ስጋዎ ተቃጥሎ እንደሚያልቅና አጥንትዎ ብቻ እንደሚቀር አጥንቱም ቢሆን ሲበዛበት እንደሚሰበር ለራስዎ ፤ ለቤተሰብዎና ለሀገርዎ ሳይጠቅሙ እንደሚተሩስ ያስታውሳሉ እንግዲያስ ስለስካር መጥፎነት የሚጠቁሙ ብዙ መጻሕፍት ስላሉ እነርሱንም መመልከት የሚከፋ አይመስለኝም ።

ከዚህ ሌላ ቶልስተይ የተባለ ደራሲ ሲናገር "ፍቅር ካለበት እግዚአብሔር ይገኛል" ሲል ጽፎአል ሌሎችም ፍቅርና እግዜአብሔር ካሉበት ደስታና ሰላም አሉ ይላሉ ይህም የማይታበል ሐቅ ነው ። ስለዚህ እርስዎም በሆነውና ባልሆነው እየተበሳጩ በመስከር የራስዎንና የቤተሰብዎን ኑሮ መራራ ማድረጉ ጥሩ አለመሆኑን ማሰብ አለብዎ ።

ለመሆኑ ምን ያበሳጭዎታል ? የሚቻልዎትን ያህል በእርጋታ መንፈስ ይሥሩ እግዚአብሔርን ከአንገትዎ ሳይሆን ከልብዎ ይመኑት ዘወትርም እርስዎና ቤተሰቦችዎ በጸሎት ትጉ ጸሎት ምን እንደተቸገርን ምን እንዳስጨነቀን በቃላት በመናገር ምንነቱን ያስታውቀናል ። ጸሎት መሰላል በመሆን ከፈጣሪያችን ጋር ያገናኘናል ።

ጸሎት የደረሰብንን ችግር ከሌላ ሰው ጋር እንዴት እንደምንካፈልና ብቻችንን አለመሆናችንን ለማወቅ ይረዳናል አንድ አስቸጋሪ ሁኔታ ሲገጥመን በቶሎ ሊያስወግደው የሚችለው የመጀመሪያው እርምጃ ጸሎት ነው ስለዚህም ብዙዎች በእውነተኛ ጸሎት እንደተጠቀሙ መጻሕፍት ያስተምሩናል ። ስለዚህ እርስዎም ከመጻሕፍት ብዙ ትምህርት ስለሚገኝ መጻሕፍትን እንዲያነቡ እጋብዝዎታለሁ በጠቅላላ ሃሳብ ደካማ አይሁኑ ። ሃሳብ ደካሞች ተስፋ መቁረጥ ስለሚገጥማቸውና የመወሰን ኃይል ስለሚያንሳቸው የመጽናናት ስሜት ያጡታቸዋል።ስለዚህም ለየትኛው ዓለም በማለት ጠጪዎች ይሆኑና ራሳቸውን ለመቆጣጠር ከማይችሉበት ደረጃ ይደርሳሉ ። በመጠጣታቸውም ደስታን የሚያገኙ ይመስላቸዋል ። እዚህ ላይ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ የነበሩት መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ ሲናገሩ ብዙ ሰዎች ደስታ ዱርዬነት ስለሚመስላቸው ደስታን ለመፈለግ በየ መጠጥ ቤት በየሆቴሉ ይሄዳሉ ደስታ ግን ዱርዬነት አይደለም በነዚህ ቦታዎች አይገኝም በነዚህ ቦታዎች የሚገኘው ደስታ ለጊዜው እእምሮን አደንዝዞ የሚናገሩትንና የሚሠሩትን እስከ አለማወቅ ደረጃ የሚያደርስ በማግስቱ የባሰ ብስጭት የሚያስከትል ነው ሲሉ ተናግረዋል ።

ስለዚህ የመጠጥ ትርፉ ይህ መሆኑን ተረድተው ደስታ የሚገኘውም በመጠጥ ቤት ሳይሆን ብዙውን ጊዜ ከውስጥ ስለሆነ መፍለቂያውና ዋናው ምንጭ እርስዎ ራስዎ መሆንዎን ማወቅ አለብዎ በትዳር ዓለም ውስጥም የሚፈለገው የመጀመሪያው ጉዳይ ሁሉንም ነገር በትእግሥት መመልከቱ መሆኑን አይዘንጉ ለሚመጣውም ከባድ ፈተና ሁሉ ሳይረበሹ በትእግሥ ያስተውሉ ። ትእግሥት የትዳር መሠረት እንዳይናጋ የሚያደርግ መሆኑን አይርሱ የብስጭትዎ መነሻ ከውጭ ከሆነም ራስ ወዳድነትን አስወግደው የእግዚአብሔርን ርዳታ በመጠየቅ ከቤተሰቦችዎ ጋር በመደሰት ሰላምን ራስዎ ይፍጠሩ ።





www.ethiopianorthodox.org

## የሴቶች ዐምድ

### ከውይይት ይገኛል ትምህርት

ከእለታት አንድ ቀን በአይሮፕላን በምንዝበት ጊዜ ብለው በመጀመር ወ/ሮ አቴልሳ የሚቀጥለውን ይናገራሉ ። እንደ አጋጣሚ የደስ ደስ ያላት በፊቷ የንዴትና የብስጭት መልክ የሚታይባት አንዲት ወጣት ወይዘሪት በጎኔ እንድትቀመጥ የአይሮፕላኑ አስተናጋጆች ጠየቁኝ እኔም ምንም ሳላቅማማ እንድትቀመጥ ፈቀድኩ ። በመጨረሻም አይሮፕላኑ በረራውን ጀመረና ስንጓዝ ጉዞአችን በጣም ረዥም ስለነበር ጎማሾቹ ማንቀላፋታቸውን ሲጀምሩ ግማሾቹ ደግሞ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን ለማንበብ ይዘጋጁ ነበር ። እኔም በበኩሌ ስለ ሰዎች ሕይወት የምትናገረውን መጽሐፌን ማንበብ ጀመርኩኝ በጎኔ የተቀመጠችው ወጣት ግን ከሃሳቧ ጋር እንደምታወራ እልፎ አልፎ በምትወረውራቸው ያልታሰቡ ቃላት ታስታውቅ ነበር ። ከቃላቱም መካከል ዘለዓለም ሳስታውሳቸው የምኖረው "ወይኔ" ትልና ቆይታ ደግሞ አይሞኝነቱ" እንደገና ቆይታ "የእጅሽን እያሳጣሽ" የሚሉ እንደነበሩ አልረሳቸውም ።

እኔም ይህች ልጅ እነዚህን ቃላት እየደገመች ስትናገር በመስማቴ ላነብ የጀመርኩትን መጽሐፍ አጠፍኩና ወጣቷን "አንቺ ልጅ ምን ሁነሻል ብቻሽን ትናገሪያለሽ የረሳሽው እቃ አለ? ወይንስ ምን የገጠመሽ ነገር አለ?" ስል ጠየቅኋት "ምንም አልሆንኩም" አለችኝ ምንም ባትሆኚ እንዲህ አትይም ነበር ብየ የተናገረቻቸውን ቃላት ነገርኳትና ይልቁንስ ድንገት ችግርሽን የማቃልልሽ እንደሆን ንገሪኝ አልኳት ወንበሯን ወደ እኔ አዞረችና ስምሽ ማነው? ስትል ጠየቀችኝ አቴልሳ ነው አልኳት ከጥቂት ሰኮንዶች በኋላ ወዴት እንደምሄድ ጠየቀችኝ ወደ አንድ የክርስቲያን ስብሰባ እንደምሄድ ነገርኳት ከዛ ስሟንና የትጽል ስሟን ነገረችኝና እንደ ሕፃን ልጅ በጣም ትናደድና ትበሳጭ ጀመር ።

እኔም የቅጽል ስሟ ሞርዛን ስለሆነ ሞርዛን ተይ አትበሳጭ እግዚአብሔርንም አታሳዝኚ ለመሆኑ ምን ሁነሽ ነው እንደዚህ የምትሆኚው ስል ደጋግሜ ጠየቅኋት ።

ሰማሽ አቴልስ ስትል አንዲት ያሳደገቻት አክስቷ እንደነበረችና ምንም እንኳን ከሕፃንነቷ ጀምሮ ያሳደገቻት ብትሆንም ይህች ሴጣት እንደነገረችኝ በብዙ ችግርና መከራ ልክ እንደ አንድ የቤት ሠራተኛ በሴትየዋ ቤት ሥርታ መግሯንና በምትበላው ምግብ እንኳን ከልጆቿ ትለያት እንደነበር በጠቅላላውም ስላሳለፈችው ችግር ነገረችኝ ይሁን እንጂ አለች ወጣትዋ እኔ ተምሬ ብዙ ተንከራትቼ ሥራ ከያዝኩ በኋላ ያንን የሕፃንነቴን ችግር ሳላስታውስ ልጆ ለወላጁ የሚያደርገውን እንዳውም ከዚያ በላይ ባለኝ ገንዘብና ጉልበት ለዛችው ላሳደገችኝ ሴትየ አገለግያታለሁ በመጨረሻ ግን በችግሯ ጊዜ ዘወር ብላ አይታት ለማታውቅ ልጅየ አዳልታ በጣም አስቀየመችኝ ይህ ሁሉ የሆነው ደግሞ አሁን ወደ ዚህ አይሮፕላን ልሳፈር ከጥቂት ሰዓቶች በፊት በንዴት ሂጄ ተነጋግረን እውነትም ብቻዬን መሆኔን አውቄ እያለቀስኩ መጣሁ፤ ስለዚህም ነው ብቻዬን ስናገር የነበርኩት አለችኝ ።

እኔም ችግሯን መረዳቴን ነገርኳትና ከአንዳንድ መንፈሳውያን መጻሕፍት ያገኘሁቸውን ምክር የቻልኩትን ያህል ነገርኳት ከምክሬም መካከል እንዲህ የሚል ይገኝበት ነበር ።

ሞርዛን ለመሆኑ ክርስቲያን ነሽ ? ስል ጠየቅኋት እርሷም አዎን አለችኝ እኔም እንግዳውስ አትበቀሉ እንደተቻላችሁ መጠን መግባባትን ፍጠሩ ይላል ቃሉ እየሽ ከሰዎች ጋር ስትኖሪ ከቶን ሁሉ አስወግደሽ በሰላም ለመኖር ሞክሪ ግን ለመኖር ብለሽ ህሊናሽ የሚወቅስሽንና ያልመሰለሽን ነገር አትሥሪ ሞርዛን ጊዜ ሲኖርሽ መጻሕትን አንብቢ ጊዜ አይቶ የማይከዳ ወዳጅ መጽሐፍ ነው ። ደግሞስ ለምን ትበሳጫለሽ ቁጣን በቁጣ በመመለስ ፋንታ ከፉን በበጉ አሸንፉ ይላል ። ሌሎች ስለ አንቺ የፈለጉትን ቢያስቡና ቢያደርጉ አንቺነትሽን አይለውጡም ። ይልቁንም አንቺ በእነርሱ ወሬ ሳትበሳጭ ጠባይሽን ሳትቀይሪ ፈጣሪሽንም በማመስገን ስራሽን መቀጠል አለብሽ።

፩ኛ ጴጥ. ም. 2 ቁ 20 ስታነቢ "ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጐሰሙ ብትታገሡ ምን ክብር አለበት ? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራ ስትቀበሉ ብትታገሡ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል ይላል ። ስለዚህ አንቺ ለእነርሱ የሚፈለግብሽን በቅን ልቡና እንኳን ፈጽምሽ እንጂ ምንም የሚቆጭሽ ነገር የለም ።

ሰማሽ እኔ ከአንቺ አላውቅም ግን ስትበደይ ነገሩን ነክሰሽ መያዝ የለብሽም እንዲያውም ይህን ያህል መናደድ አልነበረብሽም ምክንያቱም ለሰው የምታደርጊው ጥሩ ነገር ሁሉ ብድር ይመልስልኛል ብለሽ አታድርጊ በዚህ ዓለም ላይ ጥሩ ላደረገላቸው ውለታውን የሚመልሱ በጣም ጥቂቶች ናቸው አብዛኛዎቹ ግን ተመልሰው ጠላቶች ነው የሚሆኑት ። ስለዚህ ይህንን ካወቅሽ በአንችና በሌሎች መካከል ያለውን መጠነኛ አለመግባባት ዋጋ ልትሰጭው አይገባም ። ዙሪያው ሲጨልምብሽና ግራ ሲገባሽ ወደ ሰው ከመሄድ ከፈጣሪሽ ጋር በንጹህ ህሊና ብትነጋገሪ ይበልጣል መፍትሔውንም ያኔውኑ ይልክልሻል ። "እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቀውም ፣ በኋላ ግን ታስተውለዋለህ ሲል በዮሐንስ ወንጌል ተናግሯል ።

ሞርዛን በዚህ ዓለም እስከኖርሽ ድረስ ጠባይሽን የሚያስገምቱና የሚያስቆጡ ነገሮች ይደርሱብሻል ። ነገር ግን ክርስቲያንነትሽን የምታስመሰክሪው ከፉን በበጐ ስታሸንፊ ነው ። እውነተኛ ክርስቲያን ከሆንሽ ሰዎች በአንቺ ላይ መጥፎ ወሬ ቢያስወሩ ወይም ሌላ ነገር ቢያደርጉ ትዕግስተኛና ደግ የማትሰለች መሆን አለብሽ በሆነው ባልሆነው አትበሳጭ ለሁሉም ጸሎት መልካም ነው ጸልይ እንዳልኳት አይሮፕላኑ አረፈ እርሷም አይኗን አፍጣ ፊት ለፊት ትኩር ብላ እየችኝና አቴልስ አሁን ራሴን አውቄአለሁ በእውነት አንች የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው የሆንሽልኝ አለችኝ ።

እኔም እጅዋን ይዤ ልጄ እግዚአብሔርን አመስግኝ በሆነው ባልሆነው አትበሳጭ ፈጣሪሽ አሁን ምን እንደምትፈልጊ አውቋል እየሽ እግዚአብሔር እንድትጽናኚ ሲፈልግ ሳናስበው ተገናኘን እንደምታይው ስለራስሽ ማሰብ በምታቆሚበት ጊዜ አስደናቂ ነገሮች ይገጥሙሻል እኔ ራሴ በማዝንበት ስለ ራሴና ስለሌሎች ማሰቤን በመተው እግዚአብሔር መኖሩንና እርሱ ራሱ ፍቅር መሆኑን በማመን በዙሪያየ ያሉትን ደግሞ ማፍቀር እንዳለብኝ እረዳለሁ ብያት በደብዳቤ እንድንገናኝ አድራሻ ተለዋውጠን ተለያየን ። እንባብያን እናንተስ እንደሞርዛን ግራ ሲገባችሁና ስትበሳጩ ያመናችሁት ሲከዳችሁ ምን ታደርጋላችሁ ? ብዙዎቻችሁ ትበሳጩና ታለቅሱ ይሆናል ግን ጊዜና ዘመናት የማይለውጠው ፍቅሩም የማይለውጥ ሰማያዊ ጌታ እንዳለ አምናችሁ ወደ እርሱ በንጽህና ብትቀርቡ ችግራችሁ በቀላሉ ሊፈታላችሁ ይችላል ።

ብርሃን ተድላ



## ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች

ካሁን ቀደም ጽፈነው በነበረው ጽሑፍ ወንጌልን በኢትዮጵያ ለተረሱ ሕዝቦች እናስተምራለን በማለት ከተለያዩ አገሮች አዳዲስ ሐዋርያት ወይም ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ምድር ገብተው የሰጡትን አገልግሎት ማቅረባችን ይታወሳል ።

አሁን ደግሞ በአሥራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያዊው ታላቁ ሐዋርያ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አሥራ ሁለቱ ንቡራነዕድ የተባሉት ሐዋርያት በመላው ኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ ለተረሱ ሕዝቦች የወንጌልን ትምህርት እንዳዳረሱና የመንፈስ እንቅስቃሴም እንዳሳዩ ታሪክን በመመርኮዝ እናብራራለን ።

ቀደም ባለው ዘመን ወንጌል እንዳይስፋፋና፣ ዕውቀትም ለተረሱ ሕዝቦች እንዳይዳረስ በኢትዮጵያ ታላቅ ችግር ተፈጥሮ ነበር ። ይኸውም በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት የዩዲት መነሳት ነው እሷም አይሁዳዊት ስለነበረች በእጃቸው ወንጌል ይዘው ወደተረሱ ሕዝቦች ዘንድ ለማስተማር የሚሄዱትን ሐዋርያት ሕግ ተላላፊዎች ናችሁ በማለት በሞት ታስቀጣቸው ነበር የመስቀል ምልክት ያለባቸውን ም አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ በእሳት እንዲቃጠሉ ታደርግ ነበር ። ይህንንም በመፈጸምዋ በከተማም በገጠርም ያሉ ሐዋርያትና ካህናት ወደተረሱ ሕዝቦች እየሄዱ የወንጌል ብርሃን ማብራታቸው በመቀነሱ በቤተክርስቲያን ላይ ታላቅ ድክመት ደረሰ ። "መሀል ሲፈታ ዳሩ መሀል ይሆናል" እንደተባለው በመሀልም ሆነ በዳር የሚገኙ የተረሱ ሕዝቦች ሁሉ በትምህርትና በዕውቀት ብቻ ሳይሆን ኑሮአቸውም ጨለማ ሆነ ቆየ ።

ይህ ሁሉ ስቃይ አለፈና በ12ተኛው ክፍለ ዘመን በተረሱ ሕዝቦች ዘንድ ታላቅ የመንፈስ እንቅስቃሴ ተፈጠረ ። የክርስትና እምነትም ሥራ መፈንጠቅ ጀመረ ። ይህም ሊሆን የቻለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው በመጀመሪያው መልዕክቱ በምዕራፍ 1 ከቁጥር 26-28 "ወንድሞቼ ሆይ መጠራታችሁን ተመልከቱ ጥበበኞች የሆኑ ፣ ኃያላን የሆኑ፣ ባላባቶች የሆኑ አልተጠሩም ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን ለማሳፈር ድሆችን መረጠ ። ኃይለኞችንም ለማሳፈር ዝቅተኞችንና የተናቁትን መረጠ" ይላል ።

የዚህ ፍሬ ነገር ወደ ተረሱ ሕዝቦች ዘንድ ሄደው የወንጌልን ብርሃን እንዲያበሩና የክርስትና እምነትንም እንዲያስፋፉ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ጊዜ ከዝቅተኛ ቤተሰብ የመረጣቸው የተናቁትንና ከድሆች ቤተሰብ የተገኙትን ሐዋርያትን ስለነበር ነው ። በዚህም ምሳሌ ረገድ በአሥራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን በተረሱ ሕዝቦች ዘንድ እየተገኙ የዕውቀትን ብርሃን እንዲያበሩ የመንፈስ ንቃት እንዲሰጡ ከዝቅተኛና ከድሃ ቤተሰብ የተገኙትን አቡነ ተክለሃይማኖትንና አሥራ ሁለቱን ንቡራነዕድ የተባሉትን ሐዋርያት እግዚአብሔር ለሥራ መረጠ ። 12 ሐዋርያት ጎለምን በዕጣ ተከፋፍለው እየተዘዋወሩ ለተረሱ ሕዝቦች ወንጌልን ለማስተማር ሕይወታቸውን መሥዋዕት አድርገው እንዳቀረቡ ሁሉ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ሐዋርያትም ኢትዮጵያን በዕጣ ተከፋፍለው ወንጌልን ለማስተማርና የክርስትናን እምነት ለሁሉ ለማዳረስ ወደተረሱ ሕዝቦች ዘንድ ተሰማሩ ። ከነሱ ቀደም ብለው የነበሩ ሐዋርያትም ሆኑ መምህራን እንደኩሬ ውሃ ከአንድ ቦታ ተቀምጠው የእግዚአብሔርን ቃል የተጠሙ ሕዝቦች ወደነሱ እየመጡ እንዲጠጡ ከመፈለግ በቀር እነሱ የእግዚአብሔርን ቃል ወደተጠሙትም ሆነ ወደተራቡት ዘንድ ሄደው ለመመገብና ለማጠጣት ደስተኞች አልነበሩም ።

አቡነ ተክለሃይማኖትና ተከታዮቻቸው ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ዓሣ ሲያጠምዱ አግኝቷቸው ሰው አጥማጅ አደርጋችሁአለሁ" ሲል ባስተማረው መሠረት ሰውን በዕውቀትና በትምህርት ፣ በርኅራኄና በትሕትና ለማጥመድ የመጀመሪያ ጉዞአቸውን ወደ ተረሱ ሕዝቦች ዘንድ አደረጉ ።

ገድላቸው እንደሚለው አቡነ ተክለሃይማኖት በሸዋ ፣ በዳሞት ፣ በወሎ ፣ በትግራይ ፣ በኤርትራ እየተዘዋወሩ ለተረሱ ሕዝቦች ወንጌልን አስተማሩ ብዙ ሰዎችንም ወደ ክርስትና እምነት መለሱ ፣ በእጃቸውም ልዩ ልዩ ተአምራት ተፈጸሙ በተጨማሪም በወላይታ ወደሚገኙት ወደ ተረሱ ሕዝቦች ዘንድ ሂደው ወንጌልን ሲያስተምሩ ያላወቁትን ሲያሳውቁ ፣ ያልተማሩትን ሲያስተምሩ በዚያን ዘመን የወላይታ አስተዳዳሪ የነበረው ሞቶሎሚ የሚፈጽሙትን በጎ ተግባር በመስማቱ እንዲታሠሩ አደረገ በእሥራቱም ላይ ሳሉ ብዙ መከራ ቢፈጸምባቸውም የታሠሩትን እያስተማሩ የክርስቶስ ቤተሰብ አደረጉዋቸው ።

በመጨረሻ ግን ከላይ ስሙ የተጠቀሰው አስተዳዳሪ እራሳቸውን የማይወዱና ለኅብረተሰቡ እውነተኛ ትምህርት የሚሰጡ መሆናቸውን ስለተረዳው አምኖ ከነቤተሰቡ እንደተጠመቀ ይኸው ገድሉ ያብራራል ።

ቀጥለውም በወገዳ፣ በግራርያ ገዳማትን ገደሙ ወደተረሱ ሕዝቦችም ዘንድ እየተዘዋወሩ አስተምረው ካሳመኑ በኋላ እምነታቸውን እንዲያጸኑበትና ዕውቀታቸውንም እንዲያስፋፉበት በማለት ብዙ አብያተክርስቲያናት እንዲሠሩ አደረጉ

በዚያን ዘመን በትምህርት እጦት የተነሣ የጣኦት አምልኮት ተስፋፍቶ ስለነበር ይመለክባቸው የነበሩትን እያሌ የጣኦት መቅደሶችን በትምህርት ኃይል አፈረሱ ትምህርትም በመስጠት ጠንቋዮችን እያሳመኑ ብዙ የጥንቆላና የአስማት መጻሕፍት እንዲቃጠሉ አደረጉ ።

ይህም ሊሆን የቻለው በዚያ ዘመን ይኖር የነበረው ሕዝብ በትምህርት እጦት በኑሮም ተረስቶና ተገልሎ ነበር ከዚህም የተነሣ ለግል ጥቅማቸው የሚስገበገቡ አንዳንድ ካህናት አስማት እየጻፉና እየከተቡ በቁመት ሙሉ የተጻፈ የብራና ክታብ ካሠራችሁ በሽታ አይነካችሁም ፣ ከማንኛውም ችግር ሁሉ ትድናላችሁ በማለት ሕዝቡ በየአንገቱ ላይ ክታብ እንዲያስር ያሞኙት ነበር ። በሞታችሁም ጊዜ ይህን ክታብ አሥራችሁ ከተቀበራችሁ የዘለዓለም ሕይወት ታገኛላችሁ እያሉ በክርስቶስ ስም ይነግዱ ስለነበር አምልኮ ጣኦትና ክርስትና ተደበላልቆ ይኖር ነበር ።

ይህም በመሆኑ በዚያን ዘመን ክርስትናን ከአምልኮ ጣኦት የሚለዩ ሐዋርያት እንደ ተክለሃይማኖትና እንደተከታዮቻቸው እንደ 12ቱ ንቡራነዕድ ያሉ ሐዋርያት በመብራት የሚፈለጉበት ጊዜ ስለነበር እኒህን የመሳሰሉ ሐዋርያት በዚያን ዘመን መገኘት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ለምእመናን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ ታላቅ የመንፈስ ስጦታ ነበሩ ለማለት ይቻላል ።

እነዚህም ሐዋርያት ለክርስትና እምነት ለወንጌል መስፋፋት ቆርጠው የተነሱ ስለነበሩ የተረሱ ሕዝቦች ወደሚገኙበት እየተዘዋወሩ በፀጋ የወሰዱትን በፀጋ ሰጡ ይህም ተግባራቸው እምላክን ለማገልገልና የክርስትና እምነትን ለማስፋፋት ብቻ ሳይሆን ሕዝብ ከአረመኔነት ወደክርስትና ቢመለስ በኑሮም በሥራም፣ በሃሳብም እየተግባባ የወንድማማችነት መንፈስ ያድርበታል ሥራውንም ተግባብቶና ተስማምቶ በመሥራት ማኅበራዊ ኑሮውን በአንድነት ሊያካሂድ ከመቻሉም ሌላ ጠላት የመጣበትም እንደሆነ በአንድ ኅንባር ተሰልፎ ጠላቱን ለማሸነፍ እንዲረዳው ነው ።

ይህንን የመሰለ ቅዱስ ተግባር በመፈፀማቸው የልዩ ልዩ ሃይማኖት መምህራን ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት መንገድ ሲያገኙ አልቻሉም በሌላም በኩል ደግሞ አቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ ስለ ይኩኖ አምላክ የፃፉት የኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚለው "በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል ተፈጥሮ በነበረው ውዝግብ አቡነተክለሃይማኖት ስላበረከቱት መልካም አገልግሎት በሕዝብ ተተመርጠው የኢትዮጵያ ጳጳስ ሁነው ተሾሙ ከተሾሙም በኋላ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ፣ ለክርስትና እምነትና ፣ ለወንጌል መስፋፋት ለካህናቱ መተዳደሪያ በማስገኘት በኩል ታላቅ



www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖረዋል ?

ከእጅጉ ረታ

ከሃይማኖት ሥርዓት ክልል ውጭ ጾም በጤንነታችን ፣ በአካል አቋማች ንና በአስተሳሰባችን ላይ የሚጫወተው ሚና እንዳለው በቁጥር 26 ትንሜኤ ማ ቅረቢ ይታወሳል ። ጾም የአካል ቅርጽ ንና አቋምን የሚያስተካክል የሰው ነት ብርታትንና የመንፈስ ልዕልናን የሚሰጥ ፀጋ መሆኑ ከታወቀ ዘመናት አልፈዋል ። ባጠቃላይ ጾም ሙሉ ጤና ማና ደስተኛ ለመሆን ፍቱን መድኃኒት መሆኑ አያከራክርም ይሁን እንጂ ጾም ን ከማናቸውም ምግብ መከልከልን ለመጀመርያ ጊዜ በመድኃኒት መልክ የተጠቀመበት በሕክምና ሙያ ውስጥ ሥፍራ የሰጠው ማንና በምን ዘመን እንደሆነ በውል ለይቶ ለመናገር የሚ ቻል አይመስልም ። ሆኖም በጾም ታሪ ክ ውስጥ የተመዘገቡ አንዳንድ አስደ ናቂ ታሪኮችን እንደ ቅደም ተከተላቸው ቀጥለን እናቀርባለን ።

የጥንት ግብጻውያን ሙሉ ጤናማ ሆኖ እያማሩና እየሸቱ ለመኖር ቢያንስ ቢያንስ በወር 3 ቀን መጾም ማስፈለጉን ያምኑ ነበር ። በዚህም እንዳልተሳሳቱ ታውቋል ። ሄሮዶቱስ የተባለው ታሪክ ጸሐፊ ደዌ የማያውቃቸው ፍጹም ጤናማ ሕዝቦች መሆናቸውን አረጋግጦ ጽፎ ላቸዋልና ።

የጥንት የግሪክ ተወላጆች ሰውነታቸውን ከሕመም ለመጠበቅ ፣ አእምሮአቸውም በትክክል አስቦ በትክክል እንዲሠራ ለማድረግ ዋናው መድኃኒት ጾም መሆ ኑን አምነው ሲፈጽሙ ኖረዋል ።

ከዛሬ 2.400 ዓመት በፊት የነበረ ውና በዓለም ታሪክ "የመድኃኒት አባ ት" ተብሎ የታወቀው ሂፖ ክራቱስ "ለአካል የራሱ ሐኪም ያው የራሱ ተፈ ጥሮታዊ ባሕርይ ነው ። ሌላ ሐኪም የሚያረግበት ነገር ቢኖር ይህን ተግባሩን በሚገባ እንዳያከናውን የሚያውኩትን ነገሮች ቢቻል መከላከል ፣ ማስወገድ ፣ ባይቻል ማዳከምና ሕመሙ እንዲቀነስ ማድረግ ነው" ይል ነበር የመድኃኒት አባት የተባለው ሂፖክራትስ በሽተ ኛን በመድኃኒት ከሚያክምበት ጊዜ ይልቅ ለሕመምተኛ ጾምን የሚያዝበት ጊዜ እንደሚበልጥ ይነገርለታል በም ንታመምበት ጊዜ በተመገብን ቁጥር ደዌውን ማጉልበታችን ስለሆነ ፣ አካላ ችን ይብስ እንደሚጐዳ የፈረድንበት መሆናችንን ማወቅ አለብን ።

አንድ ሰው በቀን አንድ ጊዜ ብቻ የሚመገብ ከሆነ በዕድሜ ላይ ዕድሜ እ ንደሚጨምር ጥርጥር የለውም ይል ነበር ሂፖክራቱስ ። ይህንንም ራሱ ሲፈ ጽም ኖሮ እስከ ዘጠና ዓመት በላይ በዕ ድሜ የመኖርን ፀጋ ለመጐናፀፍ በቅ ቷል ።

ሶቅራጥስና ፕላቶ ጾም ለጤንነት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት ጊዜእየለዩ በየወቅቱ አስር - አስር ቀን ይጾሙ ነበር ።

ፒታጐራስ የተባለው የማቴማቲክስ (ጂዎሜትሪ) ሊቅ ጾም አእምሮን ብ ሩህ ስለሚያደርግ ለፈተና ይረዳል ብሎ የሚያምን ሰው ነበር ። ስለዚህ አንድ ጊዜ በእስክንድርያ ዩኒቨርሲቲ ጥና ቱን ለመከታተል የመግቢያ ፈተና ከመ ቀበሉ አስቀድሞ 40 ቀን በመጾም ራሱን አዘጋጅቷል ። ተማሪዎቹንም የእርሱን አብነት እንዲከተሉ በየጊዜው ያተጋ ቸው እንደነበር ታውቋል ። ፓሉታርክ የተባለ ዝነኛ ሮማዊ ጸሐፊ አንድ የታ መመ ሰው መድኃኒት ሲወስድ ያየው እንደሆነ "ለመዳን የምትፈልግ ከሆነ መድኃኒቱን ትተህ ለምን አሁኑኑ ምግ ብ አትተውም ጾም አትጀምርም" የሚ ተደርስበታል ።

በ10ኛው ና በ11ኛው ምዕት ዓመት የነበሩ የዓረብ ባለመድኃኒቶች ለቂጥ ኝና ለፈንጣጣ በሽታ የሦስት ሳምንት ጊዜ ጾም በማስጾም ያክሙ እንደነበር ተደርሶበታል ።

ናፖሊዮን በናፖርት ምድረ ግብፅን በወረረበት ዘመን ሆስፒታሎች ማና ቸውንም የአባለዘር በሽታ ለማከም የ ሚጠቀሙበት መድኃኒት ጾም ብቻ ነበር ።

ፍሬድሪክ ሆፍማን (1660 - 1742) የተባለ ጀርመናዊ ሃኪም ለሚጥል በሽ ታ (ኤፒሌፕሲ) ለአልሠር ወዘተ. ጾም ከማዘዙም በቀር ለማናቸውም ሕመም ምግብ ፈጽሞ አለመብላቱ እጅግ አስፈ ላጊ መሆኑን ገልጧል ።

በ19ኛው ምዕት ዓመት የነበሩ ሩሳ ዊው ሐኪም ዶክተር ዚላንድ ፣ የአንድ በሽተኛ የመተንፈስ ፣ የደም ማመላለ ሻና የምግብ ማዋሐጃ ሕዋሳት (ክፍሎ ች) ተግባራቸውን በሚገባ ለማከናወን እንዲችሉ ምግብ አለመመገብና ፍጹም ዕረፍት እንዲያደርጉ ዕድል መስጠት ማስፈለጉን አረጋግጠዋል "ዕረፍቱም ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎች ብቻ ሳይ ሆን ፣ የአካል ፣ የአእምሮና የመንፈስ ዕረፍትንም የሚያጠቃልል መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል" ሲሉ አስገንዝበ ዋል ።

ይቀጥላል


ምስክረ መጻሕፍት ፡-

1.ጾም ለጤንነት አስፈላጊ የሆነው ምርጥ መድኃኒት(በዶክተር አለንኩት) 12ኛ እትም (1976 ዓ.ም. እ.ኤ.አ)

2. በጾም እንዴት ጤናማና ደስተኛ ለመሆን እንደሚቻል በሳሊም ኪብራ ን እትም - 1975 ዓ.ም. እ.ኤ.አ.


አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

አቡነ ዮሐንስ የተባለው ጳጳስ ከግብጽ ተሹ ሞ በመጣ ጊዜ ግን አቡነ ተክለሃይማኖት ሥራ ን እንጂ ሹመትን የማይወዱ እየዞሩ ወንጌልን ከማስተማር በቀር ዓለማዊ ክብርን የሚጠሉ ስለነበሩ በገዛ ፈቃዳቸው ሹመቱን ለቀው እራ ሳቸውን ለሥራ ለመመደብ ወደ ደብረሊባኖስ እንደሄዱ ታሪኩ ያትታል ።

በዚህ አኳኋን አቡነ ተክለሃይማኖትን ሠራ ተኛ የሚያደርጋቸው ሌሎች መነኮሳት ሹመት ፍለጋ ደጅ ለመጥናት ከገዳም ወደ ከተማ ሲመ ጡ እሳቸው ግን ሹመት አልፈልግም ብለው ወደ ገዳም መግባታቸው ነው ።

ስለዚህ እንደ አቡነተክለሃይማኖት ያለ ሠር ቶ የሚያሠራ ፣ ክብር የማይወድ ፣ ወደተረሱ ሕዝቦች ዘንድ ሄዶ ዕውቀቱንና ችሎታውን የሚያካፍል በአሁን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ትፈ ልጋለች በእነርሱም መካከል የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደብርሃን ትታያላችሁ ተብሏልና ።

ከአለቃ ነቢየልዑል ዮሐንስ



# ዜና ሀገረ ስብከት

## ቅዱስ ፓትርያርኩ ሚትሮፖሊታን ሜቴዲዎስ ፎያንን አሰናበቱ

ሜትሮፖሊታን ሜትዲዎስ ጥቅምት 3 ቀን 1972 ዓ.ም. ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ዘንድ ቀርበው ተሰናብተዋል ። -

በተሰናበቱም ጊዜ ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ በ ኢትዮጵያና በጅቡቲ ላሚገኙት የግሪክ ኦ ርቶዶክስ አማኞች ጳጳስ ሆነው መሥራታ ቸውንና ለ11 ዓመት በጳጳስነት በቆዩበት ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስ ቲያን ግንኙነት እየተስፋፋ እንዲሄድ ከማ ድረጋቸውም ሌላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምሁራን ወደ ግሪክ ሄደው እንዲማሩ ማድረጋቸውን ፣ ተምረው ከተመለሱም መካከል እስከ ጳጳ ስነት ደረጃ ደርሰው ቤተ ክርስቲያናቸውን በማገልገል ላይ መሆናቸውን እንዲሁም ለወደፊቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲቀ ጥል ቅዱስ ሲኖዶስ ቢወስንና ውሳኔው ቢ ላክ በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በኩል የሚያስፈልገው ርዳታ እንዲደረግ የሚጥሩ መሆናቸውን ገልጸዋል ።

ሜትሮፖሊታን ሜቴዲዮስ ፎያን በእስ ክንድርያ ላለው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት ተወካይ ና ቸው ።

ሜትሮፖሊታን ሜትዲዮስ ፎያን በኢ ትዮጵያ የሥራ ጊዜአቸውን ጨርሰው የለን ደንና የታላቋ ብርታንያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሾ መው መሄዳቸውን ለቅዱስ ፓትርያርኩ ገልጸዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩም ኢትዮጵያ በቆዩ በት ጊዜ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለአደረጉት ቅን አገልግ ሎትና ለወደፊትም የሁለቱ ቤተ ክርስቲያ ኖች ግንኙነት እንዲቀጥል በማድረጋቸው አመስግነው አሰናብተዋቸዋል ።

**ደ.ማርቆስ** በጐጃም ሀገረ ስብከት ለ3 ወራት ለ50 ካህናት ጠቃሚ የሆነ መንፈ ሳዊ የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የተሰጠና ትምህርቱን የተከታተሉት ካህናት መስከ ረም 26 ቀን 1972 ዓ.ም. የተመረቁ መሆና ቸውን የደረሰን ሪፖርት አመለከተ ።

**ጂማ** ፡-በከፋ ሀገረ ስብከት ጅማ ከተማ ውስጥ ቀደም ሲል ተቋቁሞ መንፈሳዊ ሥ ራውን ሲያካሂዱ የነበረው የደብረ ሰላም ኢ የሱስ መንፈሳውያን ወጣቶች ማኅበራቸው የተቋቋመበትን 5ኛ ዓመት በዓላቸውን አክብረው ውለዋል ።

እንደዚሁም በጅማ ከተማ ለሁለት ዓመ ታት ያህል ሥራውን አቁሞ "የነበረው የመ ርሐጽድቅ ስብከተ ወንጌል" እየተባለ ይጠ ራ የነበረው መንፈሳዊ ማኅበር መስከረም 26 ቀን 1972 ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ጳጳስ ዘከፋ በተገኙበት እንደገና ሥራውን እንዲ ጀምር የተደረገ መሆኑን ከደብረ ሰላም ኢ የሱስ መንፈሳውያን ወጣቶች የተላከው ዜና አረጋገጠ ።

**ሸዋ** ፡- በሸዋ ሀገረ ስብከት በሐይቆችና ቡታ ጅራ አውራጃ በዝይ ከተማ ለ3 ወራ ት የሙያ ማሻሻያና ልማትነክ ትምህርት ለበርካታ ካህናት የተሰጠ መሆኑን ከተላለ ፈልን ሪፖርት ለመረዳት ችለናል ።

በለጠ አበበ

# ዜና አብያተ ክርስቲያናት

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልዑካን ከጄኔቭ ተመለሱ

አዲስ አበባ፡-በዓለም አብያተ ክርስቲያና ት ድርጅት የአብያተ ክርስቲያናት የልማት ተሳትፎ ጽ/ቤት ባደረገው ጥሪ መሠረት ፡-

1/ አቶ መርስዔ ኀዘን አበበ የቤተ ክህ ነት ሥራ አስኪያጅ ፣

2/ ሊቀ ካህናት ስሎሞን ገ ሥላሴ የልማ ትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ዋና ጸሐፊ ።

3/ አቶ ሻውል በለጠ የኮሚሽኑ ጉባዔ አባል መስከረም 26 ቀን 1972 ዓ.ም. ወደ ጄኔቭ ከሄዱ በኋላ በጥቅምት ወር 72 ዓ.ም. ተመል ሰዋል ። የሄዱበት ዋና ዓላማ የል ማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን እስ ከ ዛሬ ድረስ ለነበረውና ወደፊትም ስለሚ ኖረው ዓለም ዐቀፋዊ ክርስቲያናዊ ግንኙ ነት ለመነጋገርና እንዲሁም በጥር ወር 1980 (እ.ኤ.አ.) በአዲስ አበባ ከተማ ሊ ደረግ ስለታሰበው ስብሰባ ጉዳይ ለመነጋ ገር ነበር ።

## የጆርጅያ ፓትርያርክ ጉብኝት

በቅርቡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፕሬዚዳንቶች ከሆኑት አንዱ የመላዋ ጆርጅያ (ሶቪየት ኅብረት) ፓትርያርክ ብፁዕ ዳግማዊ ኤሊያ የመጀመሪያውን ይፋ



ብፁዕ ዳግማዊ ኤሊያ

ዊ ጉብኝት መስከረም 10 ቀን 1979 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) በጄኔቫ አድርገዋል ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ፊልጶስ ፓተር ሲቀበሏቸው ብፁዕ ፓትርያርኩ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ተግባራዊ ምርምርና የበለጠ አን ድነት እንዲኖር ምኞታቸውን ገልጸዋል ።

ዋን ወርልድ
ቁ 50 ጥቅምት 1979 (እ.ኤ.አ.)

## ሊቀ ጳጳስ አቴናጎራስ በረፉ

ሊቀ ጳጳስ አቴናጎራስ ፣ የታይቴይራ ሊቀ ጳጳስና በእንግሊዝ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ የነበሩት ብፁዕ አቴናጎ




www.ethiopianorthodox.org

ራበ መስከረም 9 ቀን 1979 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በሰባ ዓመታቸው በድንገት አርፈዋል። ሊቀ ጳጳሱም ከብፁዕ ሮበርት ራንሲ ጋር በአንግሊካን ኦርቶዶክስ ዶክትሪን ኮሚሽን በረዳት ሊቀመንበርነት አገልግለዋል።

ዋን ወርልድ
ቁ. 50 ጥቅምት 1979 (እ.ኤ.አ)

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለመርዳት ዓለም አቀፋዊ ውይይት ይደረጋል

ጄኔቫ ፡- ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ ክርስቲያን ለ3 ዓመታት የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ዕቅድ የወጣው 3 የቤተ ክርስቲያኒቱ ተወካዮች በጄኔቫ በተገኙበት በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ነበር። ውይይቱ፡-ከኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ/ ክርስቲያን ተወካዮችን ፣ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽንን ፣ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርን የዓለም ዐቀፍ ቤ/ ክርስቲያን ርዳታን ስደተኞችንና የዓለም አገልግሎትን እንደዚሁም በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የዓለም አቀፍ ቤ/ክርስቲያን ርዳታ ተወካዮችን ይጨምራል።

በጥር ወር 11-20 1972 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ጋር በአዲስ አበባ ከተማ የሚደረገው ጉባኤ ፡- ስለ 3 ዓመታት ከፍተኛ የልማት ፕሮግራሞች ይወያያል ። ለፕሮግራሙ የሚሆነውን ወጭ የዓለም አቀፍ ኢክዩሚኒካል ማኅበር ይችላል የውይይቱ አባላት ለጊዜው በሥራ ላይ የዋሉ የአንዳንድ ፕሮግራሞች ውጤቶችን ለማየት በኢትዮጵያ የአምስት ቀን ጉብኝት ያደርጋሉ ፤ ሲል ኢክዩሚ አካል ፕሬስ ሰርቢስ ገለጠ።

ኤክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቢስ
ቊ. 28/46ኛ ዓመት
ጥቅምት 18/1979 (እ.ኤ.አ.)

## የሉተራውያንና የኦርቶዶክስ ውይይት ለማዘጋጀት የኦርቶዶክስ መሪዎች ስብሰባ ያደርጋሉ

ሐኖቨር ጀርመን ሪፐብሊክ መስከረም 28 ቀን 1979 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ሉተራን ወርልድ ፌዴሬሽን።

ሉተራንና ኦርቶዶክስ ያለምንም ጥቅም ለብዙ ዘመናት ተለያይተው በመኖራቸው በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት በስብሰባ ለመፍታት ከመቀመጣቸው በፊት ዝግጅት መደረግ እንዳለበት የኦርቶዶክስ ዝግጅት ኮሚሽን ገልጿል።

የፓን ኦርቶዶክስ ኮሚሽን ከ16 የማያንሱ ሊቃነ ጳጳሳትንና የሃይማኖት ምሁራንን ከኮንስታንቲኖፕል ከግሪክ ከኢየሩሳሌም ከመስኮብ ከፊላንድ ከቼኮዝላቫኪያ ፣ ከሰርቢያ ፣ ከሮማንያና ከቡልጋሪያ የሚያጠቃልል ሲሆን ዝግጅቱም በማቴሪያል የተደገፈ እንዲሆንና የሚቀጥለውም ስብሰባ በእስካንዳንቪያን አገሮች መደረግ እንዳለበት ኮሚሽኑ ጠቁሞ እያንዳንዱም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በስብሰባው ላይ ተካፋይ እንዲሆን ካሳሰበ በኋላ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ ቅርሶችና የቅዳሴ ሙያ የሥራ አንድነትንም እንደሚደግፍ ገልጿል።

ከሃይማኖት ምሁራን መካከል "በ16ኛው ምዕት ክፍለ ዘመን ተደናቅፎ የቀረ ተከታታይ ውይይት በማለት አስተያየታቸውን የሰጡ ለጊዜያችንም ተስማሚና በጥሩ መንፈስም እንደሚሳካ ያላቸውን ምኞት ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ ባለፉት ጊዜያት ለሁለት ተከፍሎ የነበረው በታሪክና በዶክትሪን ውጤት መሆኑን ጠቅሶ በግልጽ ውይይት ከመካሄዱ በፊትም በውይይቱ ተካፋዮች መካከል በዶክትሪን በኩል ያለው አመለካከት ከአንድ ዓይነት ስምምነት ላይ መድረስ እንዳለበት በተጨማሪ ገልጾአል።

ኮሚሽኑን በሊቀ መንበርነት የሙሩት ጄኔቫ የሚገኘው የኮንስታትኖፕል ፓትርያርክ ተወካይ ብፁዕ ኪሚሊያኖስ ሲሆኑ እርሳቸውም በፓን ኦርቶዶክስ ኮሚሽን ሐኖቨር ተካፋዮች ለነበሩ 700 ለሚሆኑ ምዕመናን "አንዲት ቅድስት በዓለም ሁሉ ያለች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት ወይም ሕልውናዋ ያቆማል" ሲሉ አሳስበዋቸዋል።

ሉ.ወ.ፌ ኤንፎርሜሽን
መስከረም 28 ቀን 1979 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ)

## የአራት ቀን ሰሚናር በባሕር ዳር

ከገጽ ፱ የዞረ

ይት ተደርጎ ለቤ/ ክርስቲያን የሚቆረቆርና አሥራትን የሚያወጣ ሁሉ የማኅበሩ አባል መሆን እንደሚችል ውሳኔ ተላልፎአል

ከዚህ ቀደምም የማኅበሩን መቋቋም የሰሙና አላማውን የሚደግፉ ሰዎች ከልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገር አባል የሆኑ ሰዎች እንዳሉና ቁጥራቸውም በየጊዜው እየጨመረ በመሄድ ላይ እንደሆነ በማኅበሩ ሊቀመንበር ተገልጿል ።

ሴሚናሩ የተካሄደው የማኅበሩ አባላት በሚሰጡት የአሥራት አስተዋጽኦ ገንዘብ ነው ። በአንድ ዓመት ውስጥ የተደረገው የአሥራት አስተዋጽኦ ገንዘብም ከተገመተው በላይ እንደሆነ ከማኅበሩ ሊቀመንበር አንዳለጥ ለመረዳት ተችሏል።

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል ·



የከብረ ተዋሕዶ ወጣት ልጃገረዶች በመቋሚያና ጸናጽል ሲዘምሩ።



# የጤና ዓምድ

## የስኳር በሽታን እንዴት እንከላከላለን ?

የስኳር በሽታን የመቆጣጠሩ ዋና ዓላማ ከበሽተኛው ሰውነት ውስጥ ያሉትን ሁኔታዎች በትክክል ለመመልከት እስከተቻለ ድረስ በሽተኛውን ከምንምየ ሕመም ስሜቶች ነፃ ለማድረግ ነው ይህ ሊሆን የሚችለው በተመጣጠነ ምግብ በእስፖርትና ካስፈለገም መድኃኒት በመውሰድ ነው እነዚህ ሶስቱ የስኳር በሽታን ለማቃለል የምንጠቀምባቸው መሠረቶች ሲሆኑ አራተኛው ደግሞ ለበሽተኛው ትምህርት በመስጠት ነው ።

ዘወትር የምንወስዳቸው ምግቦች

ለስኳር በሽታ በብዙ ምክንያቶች በጣም ጠቃሚዎች ናቸው የምንወስደው ኃይል የሚሰጥ ምግብ ጥራትና ብዛት በደንብ የተመደበ ከሆነ የሚወስደውን መድኃኒት ሊያስቀረው ይችላል ይህም በግምት 25 0/0 የሚሆነውን ያህል በሽተኛው በተመጣጠነ ምግብ በሽታውን ሊቆጣጠረው ይችላል ።

2 ኢንሱሊን
በሚወሰድበት ጊዜ በሽተኛው ምን ያህል ምግብ እንደወሰደ ስናውቅ በደም ውስጥ ምን ያህል ግሉኮስ
እንዳለ መወሰን አይቻልም ።
3 ይህ በሽታ ትክክል
ካልሆነ ከውፍረት
የተያያዘ ነው ለእነዚህ ሁኔታዎች የተመጣጠነ ምግብ ያስፈልጋል ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ የተመጣጠነ ምግብ

አይታመንበትም ነበር በቃል የሚነገረው የስኳር በሽታ በመከላከያ በሽንት ውስጥ የሚገኘውን መጠን ያለመቆጣጠር በመቀነሱ ለበሽተኛው ቀላል አድርጎታል ይኸውም ለአንዳንድ ሐኪሞች ለችግሩ ቀላል መንገድ ሰጥቶአቸዋል ። በተዘዋዋሪ መንገድ በስኳር በሽታ የተያዙ በሽተኞች የቃል ሕክምና እየተሰጣቸው ያለምንም እርዳታ መከላከል ችለዋል ።

በዚህ መንገድ ልምድ ማድረግ በሽታው ላለበትም ሆነ ለጤነኛ በጣም ጠቃሚ ነው የተወሰደው ምግብ አይለወጥም ብለን ብንወስድ ሥራ የጉሉኮሱን መጠን ይቀንሰዋል ነገር ግን ከቀን ወደ ቀን በብዛት ሊለወጥ አይቻልም በሽተኞች ስለሚወስዱት መድኃኒት ማወቅና መማር ወይም የሚወስዱት ምግብ እንደሥራቸው መጠን መሆን አለበት ። ስለዚህ የተመጣጠነ ምግብና ሥራ ለስኳር በሽታ ዋና መመሪያዎች ናቸው ። ለበሽታው መከላከል ሌላው መንገድ በመድኃኒት መጠቀም ነው በተመጣጠነ ምግብ ወይም ከተመጣጠነ ምግብ ጋር የቃል ህክምና
መውሰድ አስፈላጊ ነው በስኳር በሽታ የተያዘ ሰው በተለይ ኢንሱሊን ይፈልጋል ነገር ግን በጉልማሳነት ጊዜ የተያዙ በሽተኞች በይበልጥ ይሰቃያሉ ኢንሱሊን የሚፈልጉ በሽተኞች ፐርሰንት ይቀንሳል ይህም ሊሆን የቻለው በዕድሜ ገደብ አማካኝነት ነው ።

ዛሬ በግምት 25 % - 30 % የሚሆኑ በሽተኞች ኢንሱሊን ይፈልጋሉ እነዚህ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ኢንሱሊንን በቀን ሁለት ጊዜ ይወስዳሉ የሚወስዱትም ለአጭርና ለረጅም ጊዜ የሚያገለግል ሲሆን ይኸም በቂ ግሉኮስ በደም ውስጥ እንዲኖርና እንዲቆጣጠርላቸው ይረዳል በተጨማሪም የኬሚካል ቅመማ ከሌሎች እንስሳ ሥጋ ይልቅ በጣም ከሰው ኢንሱሊን ጋር የተመሳሰለ ነው ይህንንም በሚወስዱበት ጊዜ ከበሽታው ነፃ እንደሆኑ ይሰማቸዋል ።

በወጣትነት በሽታው ይዞአቸው የሚሰቃዩት ዕጢ የሚሰጠውን ኢንሱሊን በማስቀረቱ ነው ሰልፎኒሉሪስ የተባለው መድኃኒት በመጠቀም ጣፊያ ደብ በማስቀረቱ ነው ሰልፎኒሉሪስ የተባለውን መድኃኒት በመጠቀም ጣፊያ ደብቆ ያቆየውን ኢንሱሊን ያነሳዋል ይህውም በጣም ጠቃሚ በመሆኑ ኢንሱሊን መርፌ መውሰድ አያስፈልግም ። የተመጣጠነ ምግብን ችላ በማለት ምክያት እንደታመነ በት ሰልፎኒሉሪስ ሰፋ ባለ ሁኔታ ወይም ሥፍራ እንደተመጣጠነ ምግብ ያገለግላል ።

የተመጣጠነ ምግብን እንደህክምና ባለመውሰድ ምክንያት ከዚህ በፊት እንደተገለፀው ሰልፎኒሉሪስ በግምት 40 - 50 0/0 የሚሆን የስኳር በሽተኞች ይጠቀሙበት ነበር በትክክል ከተጠቀሙበት በተመጣጠነ ምግብ ብቻ ሊረዱ ላልቻሉ በሰውነት ውስጥ ያለውን ሥራ በማከናወን ትልቅ ሚናን መጫወቱን ያዘወትራል ።

ትምህርት ልክ እንደመድኃኒት ሥራና የተመጣጠነ ምግብ ለዚህ በሽታ በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ጠቃሚ የሚሆኑን በሽተኞች ሕመማቸውን በደንብ ሲያውቁ ነው ሊገባቸውም የሚገባውን ትምህርት ሰፊ አድርገን ስናየው የመላው ዓለም ችግር ነው እንዲሁም ላልተስተካከለ ቁጥጥር ኃላፊነትን ይወስዳል ለመድኃኒቶች መጠን እንዳለው ሁሉ የትምህርት ዋና ዓላማ በሽተኞች በሽታቸውን በደንብ እንዲጠብቁ ማድረግ ነው ። ይህ የተሰጠው ትምህርት ለጤና መመሪያ ከበሽተኛው ችሎታ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ እንዲጠቀምበትና የተሰጠውን ምክር እንዲከተል ነውና ከሕክምና ችግር በቀር ከሐኪሞች ጋር መወያየት ከሚያስፈልጋቸው ነገሮች ትምህርቱን የሚሰጡአቸው በዚህ ሥራ ትምህርት ያገኙ ነርሶችና የጤና ሠራተኞች ሊሆኑ ይገባል ስለዚህ በሽታ የጤና ክፍል በተለያዩ የሙያ ክፍል መስፋፋትን ይጨምራል የእነዚህን በሽተኞች በእንክብካቤ በሆስፒታልም ሆነ በክሊኒክና በቤት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው ።

ንብረት አበበ



www.ethiopianorthodox.org

ooooooooooooooo **ሊቃውንቶቻችን** ooooooooooooooo

## የተዋህዶ ኃይማኖት ጠበቃ ታላቁ ሊቀ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ

**መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ የትውልድ አገራቸው ሸዋ መሆኑ ሲረጋገጥ የተወለዱበት ትክክለኛው ዓ.ም. ባለመታወቁ አልተገለጸም።**

### ትምህርት

ሊቀ ወልደ ዮሐንስ በተወለዱበት አገር የመጀመሪያውን ደረጃ ብሔራዊ ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ በጐጃም ዲማ ከአለቃ ተክለ ጽዮን ቅኔ ከመምህር ገብረ ሕይወት ትርጓሜ መጻሕፍት ተምረዋል ።

ወደ ሸዋ ተመልሰው የዓፄ ቴዎድሮስ ፍትሐ ነገሥት አውጭ ከነበሩት ከአለቃ ገብረ ኢየሱስ ዕውር ገብረ ኢየሱስ የሊቃውንት መጻሕፍት ትርጓሜ ተምረውና ዐውቀው በፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ ሙያቸው እጅግ ስመ ጥሩ ሆነዋል ።

ከትምህርት ወደ ማስተማር ዓለም ከተዛወሩ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ፍትሐ ነገሥት አውጭ የነበሩትን እነሊቁ ገብረ ክርስቶስን የመሳሰሉትን በትምህርት ወልደዋል፣ በዓፄ ምኒልክና በንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በምርምር ተልቀታቸውና በትምህርት ችሎታቸው ተመርጠው ፣ በልዩ ልዩ ወንጀል እየተከሰሱ የገንዘብ፣ የእሥራት የሞት ቅጣት በሚፈረድባቸው ሁሉ ከፍትሐ ነገሥት አንቀፁን ጠቅሰው በግዕዝ ያነበቡትን በአማርኛ ተርጉመው ሁሉ ይግባኝ የሌለበት የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጡ የፍትሕና የእውነት ጠበቃ ነበሩ።

### መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስና ታላቁ የቦሩ ሜዳ የሃይማኖት ጉባኤ

ዓፄ ዮሐንስና ዓፄ ምኒልክ /በዚያን ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ ሁለት ልደት እንዲሁም ሶስት ልደት በማለት የሃይማኖት ቅራኔ ያላቸውን ሁለት ወገኖች ልዩነት መርምረው ትክክለኛ ውሳኔ ለመሥጠት ተስማሙ ።

በዚህም መሠረት በዘመኑ የነበሩት ከፍተኞች ባለሥልጣኖች የሁለቱም ወገኖች ሊቃውንትና ካህናት በየበኩላቸው በቦሩ ሜዳ እንዲሰበሰቡ ተደረገ ።

እንግዲህ የሁለቱንም ቅራኔዎች የጥያቄና የክርክር እንዲሁም የተሰጠውን ፍርድ ዝርዝር ሁኔታ ከመተንተናችን በፊት የሚለያዩበትን የሃይማኖት ቅራኔ ግጺታ በየመልኩ ሂደት ማሳየቱ ሳይጠቅም አይቀርም በማለት ሁኔታውን እነሆ ከዚህ ቀጥሎ ገልጸነዋል ።

### ሁለት ልደት

የሁለት ልደት እምነት /ይኸውም ዛሬም ሆነ ቀድሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ የምትመራበትና ካህናትንና ምእመናንን የምትመራበት ነው። /የሚያመለክተው አንደኛ እግዚአብሔር ወልድ ቅድመ ዓለም ከአብ ፣ ያለ እናት የተወለደው አንድ ልደት ።

ሁለተኛ ድህረ ዓለም ከድንግል ማርያም እንበለ አብ በፈቃዱ የተወለደው ሁለት የልደት ይህ ብቻ መሆኑን ነው ። ሦስት ልደት የሚባለውን ግን በተዋሕዶ መምህራንም ያልተደገፈ ስለሆነ የሁለት ልደት ተከታዮች እንኳን ሊቀበሉት ሊሰሙት አይፈቅዱም ።

#### የሦስት ልደት እምነት ተከታዮች

እምነታቸው በሦስት ልደት ፈለግ ላይ የተመሠረተው ወገኖች ደግሞ

አንደኛ፡- እግዚአብሔር ወልድ ቅድመ ዓለም ከአብ የተወለደ አንድ ልደት

ሁለተኛ፡-አዳም አባታችን በንጽሐ ጠባይዕ ተፈጥሮ በመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ልጅነት ተሰጥቶት ነበር ነገር ግን በኃጢአት ምክንያት የተሰጠውን ልጅነት አጣ ።

ወደ ንስሐ ተመልሶ በሠራው በደል ስለተፀፀተም አምላክ ሥጋን ለብሶ ሰው በሆነ ጊዜ በማህፀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ አዳም አስወስዶት የነበረውን የፀጋ ልደት ተወልዶ በኩረ ምእመናን ሆነ ይህ ሁለተኛ ልደት ነው ።

ሦስተኛ፡-ከእመቤታችን የተወለደው ልደት ነው ይላሉ።

በዚህም ሁኔታ በየጊዜው በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የተዋህዶ ወገኖች የነገሥታቱን ድጋፍ ሲያገኙ የፀጋ ልጆችን፣ የፀጋ ልጆችም ጊዜ ሲያመቻቸው የተዋህዶ እምነት ተከታዮችን በማጥቃትና በማሳደድ የርስ በርስ ቁርቋስ በማድረግ አያሌ ጊዜ አሳልፈዋል ።

### የሁለቱ ወገኖች የክርክር ስልትና የተሰጠው ፍርድ

ከላይ እንደተመከተው ሁሉ ሁለት ነገሥታትና እጨጌው ባሉበት ከፍተኞች ባለሥልጣኖችና ሊቃውንቱ በተሰበሰቡበት ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጐ ተከራካሪዎቹ ግራና ቀኝ ሊቋቋሙ እጨጌ ቴዎፍሎስ የሁለት ልደት እምነት ተከታዮች በቆሙበት በኩል ወንበር ተዘርግቶላቸው ለክርክሩ ሲሰለፉ እንግዲህ ተከራካሪያችሁ እኔ ነኝ ሲሉ ለሦስት ልደት ወገኖች ማለት ለፀጋ ልጆች አስረዱ ።

ተከራካሪዎቹ ከሁለት ልደት እምነት ወገኖች አለቃ ኪዳነ ወልድ ፣መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስና አለቃ ተክለ ሥላሴ ሲሆኑ ከሦስቱ ልደት ባዮች ወገን ደግሞ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ አለቃ ሀብተ ወልድ ፣ አለቃ ውቤና አለቃ ቤተ ሎሚ ነበሩ ።

አለቃ ተክለ ጽዮንም ለሦስት ልደት ተከታዮች ተከራካሪ ለመሆን ወደቦሩ ሜዳ ሔደው ነበር፣ ነገር ግን የሦስቱን ልደት ባህል ከመከተልም አልፈው በሁለት ባህርይ የእምነት ስልት የሚመሩ መሆናቸውን ዓፄ ዮሐንስ ቀደም ብለው ተገንዝበውት ኖሮ ለመሆኑ ተክለ ጽዮን ከሊቃውንቱ ጋር ወደዚህ ጉባኤ መጥቶአልን ? ብለው ሲጠይቁ ዓፄ ምንሊክ ስለሰሙ አይለቁህምና በቶሎ እጅህን አውጣ ብለው በምሥጢር ለአለቃ ተክለ ጽዮን ነግረዋቸው ከጉባኤው ተደብቀው እንዳመለጡ ይነገራል ።

ሆኖም በዚህ ዓይነቱም ምክንያት አለቃ ተክለ ጽዮን በክርክሩ መድረክ ተገኝተው የሚያቀርቡት ጥያቄና የሚሰጡት ኃይለ ቃል ሳይሰሙና ሳይታወቅ በመቅረቱ ብዙዎች የታሪክ ተከታዮች አዝነውበታል ።

ከዚህ በኋላ የመጀመሪያው ጥያቄ ለሁለት እምነት ልደት ተከታዮች ሊቃውንት ሆና በቀድሞው የሙገት ልማድ በተጠየቅ ስልት ክርክሩ ቀጠለና አፈ ጉባኤው አለቃ ኪዳነ ወልድ ተጠየቅ ልጠይቅህ ሲሉ የሦስት ልደት ወገኖች አፈጉባኤ ሆነው የቀረቡት አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ እሺ ልጠየቅ ሲሉ መለሱ ጥያቄ = ሥላሴ በአካል ሦስት ናቸው መልስ አዎ ሦስት ናቸው ጥያቄ በክብር ትክክል (ዕሩያን) ናቸው አይበላለጡም ? መልስ አዎ አይበላለጡም ጥያቄ ሥላሴ በከዊን ሀልውና ከመገናዘብ በቀር አንዱ አካል በአንዱ አካል አያድርም ? መልስ አዎን አያድርም ስለአሉአቸው አለቃ ኪዳነ ወልድ ለጥያቄአቸው ያገኙት መልስ ትክክለኛ አቅጣጫ መያዙን ተገንዘቡና እንዲህማ ከሆነ አንተና ተከታዮችህ ከራሳችሁ አንቅታችሁ ከሦስቱ አንዱ አካል ቃል ሥጋ በሆነ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ አደረበት ፣ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የፀጋ ልጅ እያልክ ታስተምራለህ ? ሲሉ አከታትለው ለውሳኔ የሚያመች ጥያቄ አቀረቡ በዚህ ጊዜ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ መልስ ሳይሰጡ ዝም አሉ ።

ዋልድቤ እንግዳና ዙርአምቤ እንግዳ የተባሉ ሁለት መነኩሳት ግን ከአለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ጋር ቆመው ነበርና ሁለቱም ባንድ ቃል ስለ ሦስት ልደት ባህል በድፍረት ተናገሩ በዚህ ጊዜ ዓፄ ዮሐንስ ቢቆጡ እጨጌ ቴዎፍሎስ ጃንሆይ ዳኝነት ብቻ ይሰሙ እንጂ አይቆጡ ሲሉ አሳሰቡ ፣ ቀጥለውም አለቃ ተክለ ሥላሴ ለአለቃ ኪዳነ ወልድ ረዳት ሆነው ልዩ ልዩ ጥያቄ አቀረቡና መልስ ተሰጣቸው ።

ከዚህ ቀጥሎ ሦስተኛ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስንየሚከተለውን ጠየቁአቸው ። ጥያቄ የመንግሥት ገንዘብ በሚገባ ተቆጥሮ በመዝገብ ይጻፋል ? መልስ አዎ ይጻፋል ጥያቄ በመዝገብ ከተጻፈው ያተረፈም ያጎደለም ይቀጣል ? መልበ አዎን ይቀጣል ጥያቄ የሥላሴ ገንዘባቸው ሃይማኖት ነው ? መልስ አዎ ገንዘባቸው ሃይማኖት ነው ።ጥያቄ የሥላሴ ገንዘብ ሃይማኖት ተሰፍሮ ተቆጥሮ በመዝገብ ተጽፎአል ? መልስ አዎ ተጽፎአል ጥያቄ ከመጻሕፍት ቃል ያተረፈም ያጎደለም ይቀጣል ? መልስ አዎ ይቀጣል ጥያቄ መጽሐፍ ነአምን ክልኤተ ልደታት ብሎ በአኃዝ ወስኖ ነግሮናል መልስ አዎ መጽሐፍ ነአምን ክልኤተ ልደታት ይላል ።

እንደዚህ ያለ የተስተካከለ መልስ የተሰጣቸው መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ከመጽሐፍ ቃል ያተረፈም ያጎደለም የሚቀጣ ከሆነ መጽሐፍ ወስኖ ነአምን ክልኤተ ልደታተ ብሎ ከተናገረ አንተ ግን ከዚህ አልፈህ ተርፈህ ሦስት ልደት እያልክ ስታስተምር ከተገኘህ ? አንተም ተከታዮችህም ትቀጡልኛላችሁ ሲሉ ውርድ ነዙ። በዚህም ጊዜ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ተጠየቅ ስለአሉ ዓፄ ዮሐንስ ሊታሳስቱኝ ነው ? ተጠየቅ ይቅርና ወልደ ዮሐንስ ነአምን ክልኤተ ልደታተ ብሎ እንዳስረዳው አንተም ሦስት ልደት የሚል ደረቅ ንባብ አምጣ ብለው ስለ ተናገሩ የሁለት ልደት ወገኖች እየተፈራረቁ ጠይቀው የሦስት ልደት ተከታዮች ጥያቄ ሲከለከሉ ዳኝነት ይጉድል የለምን ? ብለው በጉባኤ ከነበሩት አንዳንድ ሰዎች ስለአሳሰቡ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ እንዲጠይቁ ተፈቀደና መልአከ ብርሃን ወልደዮሐንስን የሚከተለውን ጠየቁአቸው ጥያቄ እናትና ልጁን ልደት እንጂ ያገናኛቸዋል ? መልስ አባዬ! አባዬ! ያራዳ መምህር! የእሷ ልደት በሩካቤ በዘርዕ፣ የእሱ ልደት እንበለ ዘርዕ ምን አገናኛቸውና አሉ ።

በዚህም ጊዜ የፀጋ ልጆች ሌላ ማስረጃ ሊጠቅሱ ባለመቻላቸው ከምእመናን በመለየት በግዝት፣ እንዲቀጡ ተፈረደባቸው በመፀፀት የተመለሱትም ንስሐቸውን እንዲያደርሱ ሆኖ ምህረት ተደረገላቸው ።

መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ በትምህርታቸውና በአስተዋይነታቸው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ግምታቸው እየላቀ ስለታየ መልአከ ብርሃን ተብለው የደብረ ብርሃን ሥላሴን እንዲሁም የአዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤልን ደብር ሲያስተዳድሩ ሲያስተምሩና ፍትሐ ነገሥት ሲያወጡ ከቆዩ በኋላ በ1906ዓ.ም. ታኅሣሥ 18 ቀን አርፈው በመንበረ ፀቦያት ቅድስት ሥላሴ ተቀብረዋል ።

ማስገንዘቢያ

ሊቃውንቶቻችን በማስተማር ብዙዎችን በሃይማኖት ማስተባበር ሲገባቸው እሐቲ በተባለች ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ የሃይማኖት ስልት እየፈጠሩ እርስ በርሳቸው ሲጣሉና ካህናቱንና ምእመናኑን ግራ ሲያጋቡ መኖራቸው አሳዛኝበመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ዛሬም ሆነ ወደ ፊት ይኸንን ከመሰለው አድራጎት እንድትጠበቅ በዚህ አጋጣሚ መልእክታችንን እናስተላልፋለን ።

አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

## የአራት ቀን ሰሚናር በባሕር ዳር

ከገጽ ፲፮ የዞረ

በሴሚናሩም የተገኙ አባቶች በሚቻለን ሁሉ አላማው ግብ እንዲመታ ከማኅበሩ ጋር እንሰለፋለን” በማለት ቃል ገብተዋል ። በሴሚናሩ መጨረሻ ቀንም የሴሚናሩ አዘጋጅ ክፍል አንድ መርከብ ተኩናትሮ የሴሚናር ተካፋዮችን በሙሉ ጥንታውያን ቅርሶች የሚገኙባቸውን ሁለት ቦታወች ኡራ ኪዳነምህረትንና ክብራን ገብርኤልን አስጐብኝቶአል ። በጉብኝቱ ጉዞ ላይ የማኅበሩ መዘምራን ልዩ ልዩ መዝሙሮችን በመዘመር ለሴሚናር ተካፋዮች የመንፈስ ደስታ ሰጥቶአቸው ነበር ።

ከዚያም ከጉብኝቱ መልስ የስንብት ጸሎት ተደርጐአል ። መዘምራንም ሰንብትን የተመለከተ መዝሙር አቅርበው በሰሚዎች ልቡና የማይጠፋ ትዝታ አሳድረዋል ። ሁሉም አባላት “እግዚአብሔር ለመጭው ዓመት የስብሰባ ጊዜ ያድርሰን” በማለት የመጨረሻ ስንብት አድርገዋል ።

ከዚህ ቀጥለን ከሴሚናሩ ተሳታፊዎች መምህራን አንዱ መሪጌታ ከአቀረቡአቸው ግጥሞች ጥቂቶችን እናቀርባለን ።

መናፍቃን ቀርበው ቢከራከሩዋችሁ
የምትመልሱት አያስብ ልባችሁ
ጌታችን ብሎናል እኔ ነኝ አፋችሁ
የክርክርማ ብዙ ነው መንገዱ
ለኛ ይበቃናል ነአምን በአሐዱ
ለምን ይሆናል ሰው እምነተ ጐደሎ
የልቡናን እምነት ሳያይ አስተውሎ
ቁሱን ይለምናል እምነት ይስጡኝ ብሎ
እምነቱን ቆንጥሮ ቁሱም እንካ ቢለው
ደግሞ መቋጠሪያ መያዣ ጠየቀው
ቁሱም ሳያስተውል ቸኩሎ ለሥራው
የእምነት መቋጠሪያ ልብ ነው እንዳይለው
እንደ እሱ ጥያቄ ግምጃ ቀዶ ሰጠው
ይህ ዓይነት ጥያቄ ቁሱን ቢያሰለቸው
ስለ እምነት ማስተማር ማስረዳት ሲገባው
የማያልቀውነን እምነት አልቋል አለው
ካልተጨመረበት የልባችን እምነት
መዳን አይገኝም እምነቱን ቢቀቡት
ሳንጠራጠረው እንመን በኢየሱስ
ከሕማማችን ቶሎ እንድንፈወስ
አልቋል ጥርጥሩ በነዘካርያስ
ጌታችንም ብሏል ስሙኝ ልንገራችሁ
ትንሽ ቅንጣት ያህል እምነት ቢኖራችሁ
ተራራውን ሁሉ መናድ በቻላችሁ ።





www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ከክንፈ ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብዙ የወጣቶች መንፈሳዊያን ማህበራት የተቋቋሙ እንዳሉ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው።

የወጣቶች ማኅበራት ከሚባሉትም አንዱ ማኅበር መንእሰይ ፍኖተ ብርሃን ነው ይህ ማህበር ከተቋቋመ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ምን ያህል ክርስቲያናዊ ሥራ እንዳከናወነ የማህበር መንእሰይ ፍኖተ ብርሃን ዋና ጸሐፊ አቶ ሲሳይ ንጋቱን ጠይቀናቸዋል።

ትንሣኤ ማህበር መንእሰይ ፍኖተ ብርሃን ከተቋቋመ ስንት ይሆነዋል ያቋቋሙት አባሎች እየጨመሩ ናቸው ወይስ ተቀንሰዋል።

አቶ ሲሳይ ንጋቱ ይህ በአሥመራ ከተማ የሚገኘው ማህበር መንእሰይ ፍኖተ ብርሃን ከተቋቋመ 27 ዓመት ሁኖታል የማህበሩ አባሎች ግን በርከት ያሉ ቋሚ ማህበርተኞች ያሉት ሲሆን አሁንም የማህበርተኞቹ ምዝገባ እየቀጠለ ነው ማህበር መንእሰይ ፍኖተ ብርሃን በኤርትራ ክፍለ ሀገር ግንባር ቀደም ሆኖ ኦርቶዶክሳዊ እንቅስቃሴን እያካሄደ እጅግ በጣም በርከት ያሉ ምእመናን እንደዚሁም ወጣቶች ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክና የቅዱስ መጽሐፍን ትምህርት በማስተማር አገልግሎአል። አሁንም በማገልገል ላይ ይገኛል።

ትንሣኤ፡ ማህበር መንእሰይ ፍኖተ ብርሃን ሥራውን የሚያካሂድበት የገቢ ምንጭ አለው ወይ? በሚያገኘውስ ገቢ ምን ሰርቶበታል።

አቶ ሲሳይ ቀዋሚ ባጀት የለውም ነገር ግን በተለያዩ ዘዴዎች ትንሽ ገቢ እናገኛለን ለምሳሌ በ1963 ዓ.ም. በአሥመራ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ ለስብከተ ወንጌልና መንፈሳዊ አገልግሎት የሚረዳ አንድ የስብሰባ አዳራሽ እንዲሠራ ባደረገው እቅድ የአንድ / ሺህ / 1000 ብር ሎተሪ ለሽያጭ በማውጣትና ልዩ ልዩ መንፈሳዊያን ቲያትሮችን እንዲሁም ፊልሞችን በማዘጋጀት በሌላም በኩል ማህበሩ በሚያደርገው አስተዋጽኦ ማህበርተኞቹ ከሚያደርጉት ወርሃዊና ሳምንታዊ መዋጮ ሌላ ከአንድ መቶ አምሳ ሺህ ብር /ከ150/ ሺህ የኢትዮጵያ ብር በላይ ባገኘው እርዳታ የሚከተሉትን ሥራዎች ሠርቷል።

1ኛ/ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰዎች ለመያዝ የሚችል ትልቅ አዳራሽ ሁለት የጽሕፈት ቤቶች አንድ ሰፊ ቤተ መጻሕፍት እንዲሁም አንድ ሰፊ የመዝናኛ ክፍል አራት የመጸዳጃ ክፍሎች ሁለት መጋዘኖች ሁለት የመዘምራን መሰብሰቢያ ያሠራ ሲሆን በመካከሉም የገንዘብ እጥረት ደርሶበት ለሕንጻው ሥራ ማስፈጸምያና ለማህበሩ ሥራ አገልግሎት ማስፋፊያ የሚሆን የእርዳታ ገንዘብ እንደ ሚያስፈልገን ተገንዝበን ያጋጠመንን ችግር በመግለጽ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን የልማት ኮምሽን በኩል የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማህበር በእርዳታ ገንዘብ እንዲሰጠን ጠይቀን ከብዙ ድካም በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ከፍተኛ ጥረትና ድጋፍ ገንዘብ ደርሶን በአሁኑ ጊዜ የሚያስፈልገን ሁሉ በሟሟላት ላይ ስለምንገኝ በዚህ አጋጣሚ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ባደረጉልን ከፍተኛ ድጋፍና መንፈሳዊ ትብብር ለቅዱስነታቸው ከልብ የመነጨ ምሥጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን በዚህ አጋጣሚ ልናገረው የምፈልገው ይህንኑ የሕንፃችን ሥራ እንዳጠናቀቅን ቅዱስነታቸው እንደሚጎበኙልንና እንደሚባርኩልን ተስፋ እናደርጋለን።

እንዲሁም በቅዱስነታቸው መልካም ፈቃድ የሚከፈት አንድ አገር አቀፍ መንፈሳዊ ሴሚናር በልማት ኮምሽን ተባባሪነት በማህበራችን ስብከተ ወንጌልና ጸሎት አዳራሽ ውስጥ እንዲካሄድ ከተፈቀደ ከፍ ያለ ፍሬ ይገኝበታል ብለን ጽኑ እምነትና ምኞት አለን።

ትንሣኤ፡ ማህበሩ ከዚህ በፊት መንፈሳዊ ሥነ ጽሑፎችን እያዘጋጀ በጋዜጣ እያሳተመ ለምእመናን ያደርስ እንደ ነበርና በኋላም እንደቆመ ይታወሳል የቆመበት ምክንያት ምን ነበር?

አቶ ሲሳይ አዎ ማህበራችን ፍኖተ ብርሃን የተሰኘውን መንፈሳዊ ጋዜጣ በየወሩ አንድ ጊዜ እያሳተመ ለረጅም ጊዜ ሲያገለግል ነበር በኋላ ግን ከመንግሥት ሲሰጠው የነበረው ድጐማ ስለተቋረጠ በገንዘብ እጥረት ቆሞ ነበር አሁን ግን ቸርነት ገንዘቡ የሆነ ልዑል እግዚአብሔር ከማህበራችን መካከል ሁለት በጎ አድራጊዎችን ስላነሣልን ጋዜጣውን ለማሳተም ቃል በገቡልን መሠረት ካለፈው መስከረም ወር 1972 ዓ.ም. ጀምሮ ማሳተም ጀምረናል። እንዲያውም ፍኖተ ብርሃን የተሰኘው ጋዜጣችን በምእመናን በኩል ከፍተኛ ተወዳጅነት ያለው መንፈሳዊ ጋዜጣ ቢሆንም ሁሉም እንዲገዙ በማሰብ በዝቅተኛ ዋጋ ስለሚሸጥ ለኪሣራው መሸፈኛ በየጊዜው ከበጎ አድራጊዎች እርዳታ እንዲደረግለት ከመጠየቅ ይልቅ አንድ ዘላቂ መፍትሄ እንዲገኝለት አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ ላይ ስለሆነ የመንበረ ፓትርያርኩ ጠ/ ጽ/ቤት የስብከተ ወንጌልና ማስታወቂያ መምሪያ በኩል ድጋፍ እንዲሰጠን ጽኑ እምነት ስላለን ጋዜጣው ለወደፊት እንደሚታተም ተስፋ አለን።

ትንሣኤ፡ በማህበሩ ሥር የሚተዳደሩ ድርጅት አሉ?

አቶ ሲሳይ እቅዳችን በጣም ሰፊ ነበር ይኸውም ከዚህ በፊት በክፍለ ሀገሩ ዋና ከተማ በአሥመራ ብቻ ሳይሆን በየአውራጃ ቅርንጫፍ ለማቋቋም ከፍተኛ ጥረት አድርገን ነበር ሆኖም ጊዜው አመቺ ባለመሆኑ ባሁኑ ጊዜ በማህራችን ሥር የሚተዳደሩ ድርጅት የሉንም ለወደፊት ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ በክፍለ ሀገር በአውራጃዎችና በወረዳዎች መልሰን በማቋቋም መንፈሳዊ ተግባራችንን ለማጠናከር ጥረት ለማድረግ ሰፊ ሐሳብ አለን።

ትንሣኤ፡ ማህበሩ ከጋዜጣው መቋረጥ ሌላ ምን ችግር ነበረበት?

አቶ ሲሳይ ማህበራችን እስካሁን ድረስ ያጋጠመው ችግር የለውም ከዚህ የተነሣ ማህበራችን በአሁኑ ጊዜ በሚያስደስት ሁኔታ ነው የሚገኘው መንፈሳዊ አገልግሎትም በማከናወን ይገናኛል። ለወደፊትም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት በተሰጠን የእርዳታ ገንዘብ አማካይነት የሠራነው የልማት ነክ ሥራ ለወደፊት በጋዜጣ እንዲገለጽ እናደርጋለን ይኸውም በአሁኑ ጊዜ ከግማሽ በላይ የሠራነው ቢሆንም ቀሪው ሥራ እንደተጠናቀቀ ሥራውን በስዕል ጭምር አውጥተን እንገልጻዋለን ሲሉ አብራርተዋል።



# ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ



ከአሁን ቀደም እንደተገለጸው ሥነ ጽሑፍ ቋንቋን አምልኮን እቅፎ የሚራመድ እንደመሆኑ መጠን እልም ብልጭ እያለ እስከ ዘመናችን ደርሷል ከልደተ ክርስቶስ አንስቶ አሁን እስካለንበት ክፍለ ዘመን ድረሥ ሥነ ጽሑፍ የተስፋፋባቸው ዘመናት ሲኖሩ በዚያው አንፃር ደግሞ እንዲጠፉ የተደረገባቸው ዘመናት ነበሩ።

ለምሳሌ በዮዲት፣ በግራኝ መሐመድና በመሳሰሉት ኢ አማንያን ዘመነ መንግሥት ሥነ ጽሑፍ በእሳት እንዲቃጠል ሲደረግ ጸሐፍቱም እየተፈለጉ እንዲገደሉ ተደርጎ ነበር፣ ነገር ግን በዓፄ ገብረ መስቀል፣ በይኩኖ አምላክ፣ በዓመደ ጽዮን፣ በዘርዓ ያዕቆብና በመሳሰሉትም ሀገር ወዳድ መሪዎች ዘመነ መንግሥት ሥነ ጽሑፍ እጅግ በጣም እየተስፋፋ መሄዱን ከታሪክ እንረዳለን።

የሀገራችንን ሥነ ጽሑፍ ግደግና ግነስ በምንመለከትበት ጊዜ ለሥነ ጽሑፍ መስፋፋት ቅን አስተያየት የነበራቸውንና ራሳቸውም ደራሲያን በመሆን የረዱትን የጊዜው መሪዎች አክሎ መጥቀሱ አስፈላጊ መስሎ ታይቶኛል በእርግጥ ሁሉንም መሪዎች ከእንሕይወት ታሪካቸው አቀንባብሮ በዚሁ ጽሑፍ ለማቅረብ አይቻልም። ቢሆንም ለሀገራቸው ሥነ ጽሑፍ የደከሙትን መሪዎች በአጭር አዘጋጅቶ ለአንባብያን ማቅረቡ የሚከፋ አይመስለኝም።

በሀገራችን ሥነ ጽሑፍን በዘመነ መንግሥታቸው አስፋፍተዋል ከሚባሉት ጥቂቶች ዓፄ ገብረ መስቀል፣ ላሊበላ፣ "ይኩኖ አምላክ ዓምደ ጽዮን ዘርዓያዕቆብ ኢያሱ አዲያም ሰገድና የመሳሰሉትም ናቸው ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ባለሥልጣኖች አንድ ባንድ ስንመለከታቸው የሥነ ጽሑፍን እርምጃም በመጠኑ ለመረዳት እንችላለን። በመጀመሪያ ዓፄ ገብረ መስቀል፣ ዘመኑ ስድስተኛው መቶ ዘመን ነው በዚህ ዘመን ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማዎችን የደረሰበት ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ሀገራችን የገቡበት ነው፣ የቅዱሳኑ ስምና የመጡባቸው ሀገሮች

1- አባ አረጋዊ ዘሚካኤል ከሮም

2- .. ጳንጠሌዎን

3- .. ገሪማ /ይስሐቅ/ ከሮም

4- .. ሊቃኖስ ከቁስጥንጥንያ

5- .. ይምዓታ ከቆስያ /ከሲስሊ/ ኢጣሊያ

6- .. ጽሕማ ከአንጾኪያ ከሶርያ

7- .. አባ ጉባ ከቂልቅያ ግሪክ

8- .. አሌፍ ከቂሣሪያ

9- .. አፍጼ ከእስያ የመጡ ሲሆኑ እነዚህ ቅዱሳን ወደ ሀገራችን የመጡት በየሀገራቸው ተነሥቶ በነበረው የሃይማኖት አለመግባባት ምክንያት መሆን ባይካድም ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ቀን ጀምሮ ዝም ብለው አልተቀመጡም በመጀመሪያ ሐዋርያው ፊልጶስ ከእርሱም ቀጥሎ አባ ሰላማ ፍሬምናጦስ ያስተማረውን የክርስትና እምነት በየአውራጃውና በየወረዳው ተበታትነው ከማስተማራቸውም ሌላ ቅዱሳት መጻሕፍትንም እየጻፉ ለየአድባራቱና ገዳማቱ በሰፊው እንዲዳረሱ አድርገዋል።

ከ9ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ እስከ ይኩኖ አምላክ ዘመን ድረስ ይህም 13 ተኛው መቶ ዘመን መሆኑ ነው በእነዚህ ዘመናት እነዚህ ቅዱሳን የጻፉት ጽሑፍና የተጻፈላቸው ገድል ከኢትዮጵያ አልፎ በውጭ ሀገር በፓሪስ በለንደንና በሮም ቤተ መጻሕፍት እንደሚገኙ የታሪክ ሊቃውንት በጽሑፋቸው ጠቅሰው ተናግረዋል ከዚያም የአባ ገሪማንና የአባ ጳንጠሌዎንን በሮማ ቤተ መጻሕፍት ኮንቲ ሮሲኒ የአቡነ አረጋዊን ገድል ኢኛስዩጓዲ አሳትመውታል የሚለው በተጠቀሰው ክፍለ ዘመን ነው።ከላስታ ዘመነ መንግሥት ወዲህ በይኩኖ አምላክ ዘመን የሥነ ጽሑፍ ይዞታ ለየት ባለ መንገድ መስፋፋቱን ቀጥሏል በዚያ ዘመን ለብዙ ዘመናት በኖረው በግዕዝ ቋንቋ ፋንታ ለሕዝብ ሁሉ በጠቅላላ መነጋገሪያ እንዲሆን የአማርኛ ቋንቋ ተተክቷል፣ መጻሕፍትም ከግዕዝ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ በብዛት እየተተረጐሙ ሁሉም እንዲያነባቸው ተደርጓል ይኩኖ አምላክ መንግሥቱን እጅ ካደረገ በኋላ ቅድሚያ የሰጠው ለቤተ ክርስቲያን ተግባር ነበር።

ዘአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የሚሆን ከመንግሥቱ ገቢ ሲሶውን ሲሰጥ ቅዱሳት መጻሕፍትም እየተጻፉ ለአድባራቱና ለየገዳማቱ እንዲደርሱ በማቀድ ብዙ ሊቃውንትን ሰብስቦ አጽፎ አሠራጭቷል ከእርሱም ቀጥሎ ሥነ ጽሑፍን ለማስፋፋት ሰፊ መንገድ ን ከፍቶ የነበረው አፄ ዓምደ ጽዮን ነው ዓምደ ጽዮን በአስተዳዳሪነቱና በጀግንነቱ እጅግ በጣም የተመሰገነ ከመሆኑም ሌላ የታሪክና የሥነ ጽሑፍንም ጥቅም በማወቁ ወደ መረሳቱ ተቃርቦ የነበረውን የአክሱምን ታሪክ ነገሥት በመጻፍ መንገድ የከፈተው እርሱ ነው። እንዲሁም ቤት እየሙቱ ግጥም እያሰናዱ ስንኝ መጻፍ የተጀመረው በዓምደ ጽዮን ዘመን መሆኑ ይነገራል ዓምደ ጽዮን ሃይማኖተ ብርቱ ጀግና ከመሆኑ የተነሣ ወደ ጦርነቱ ለመሄድ ሲዘጋጅ ም ሆነ ድል አድርጐ ሲመለስ የሚጸልያቸውን የጸሎት መጻሕፍትን በርከት አድርጐ መድረሱ ይነገርለታል።

ሥነ ጽሑፍ የተስፋፋበት ሌላው ክፍለ ዘመን የዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ነው፣ ዘርዓ ያዕቆብ ጣዖታትን ለማጥፋትና ሥነ ጽሑፍን ለማስፋፋት የነበረው ፍላጎት ከፍ ያለ ስለነበር ከክርስትና እምነት ውጭ የዛፍ የአድባር የመናፍስት እንዲሁም ልዩ ልዩ አምልኮ ይዞ ይጓዝ የነበረውን ሕዝብ ለማስቀረት በሥነ ጽሑፍም በአዋጅም በቅጣትም መልክ የፈጸመው መንፈሳዊ አገልግሎት በቀላሉ የሚገመት አይደለም በሀገራችን ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥትን ለማገልገል የሚችሉትን መጻሕፍት የሚገልጽልን ታሪክ ነገሥት ነው ይሁን እንጂ ከግዕዝ ቋንቋ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለአንባቢያን ባለመቅረቡ ከፍ ያለ ችግር ስለነበር ዘርዓ ያዕቆብ ችግሩን በመገንዘብ መጽሐፉ በእጅ ጽሑፍ እየተባዛ ለአንባቢያን እንዲዳረስ አድርጓል ዘርዓ ያዕቆብ በየሳምንቱ ቅዳሜ እሁድ እንዲከበር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓል በየወሩ በ29 ቀን፣ የእ



www.ethiopianorthodox.org

መቤታች ድንግል ማርያም በዓል በዓመት 33 ቀን እንዲከበር የቅዱስሚካኤል በዓል በየወሩ የካህናተ ሰማይና የአርባዕቱ እንስሳ የሐዋርያትም በዓል በዓመት አንዳንድ ቀን እንዲከበር በመጽሐፍ አጽፎ ለየአድባራቱ አሰራጭቷል ።

ዘርዓ ያዕቆብ የጻፋቸው መጻሕፍት ስማቸው የሚከተለው ነው ። ሀ/ ጦማረ ትስብእት ለ/ መ/ ብርሃን ሐ/ መ/ ምዕላድ መ/ከህደተ ሰይጣን ሠ/ መ/ባህርይ ረ/ ተዓቅቦ ምስጢር ሰ/ እግዚአብሔር ነግሠና ወዘተ ናቸው በተጨማሪም በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ከዚያም በላይ ድርብ ታቦት እንዲቀመጥ ሲወሰን ታቦታቱ ሁልጊዜ ከእመቤታችን ጽላት ጋር አብረው እንዲገኙ ናበሁለቱ የሰንበት ቀናትና በሌሎችም የከብረ በዓል ቀናት ወንዱም ሴቱም እየተሰበሰበ ካህናቱ ጸሎተ ሃይማኖትን ጸሎተ ወንጌልን 10ቱ ቃላተ ኦሪትን 6ቱ ቃላተ ወንጌልን እንዲያሰሙ ምስጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ሥጋዌን ሁልጊዜ ካህናት በየሥፍራው ለሚገኙ ሰዎች እንዲያስተምሩ ካህናት በየቦታው ይህንን ባያስተምሩ ቤታቸው እየተበረበረ ገንዘባቸው ይወረሳል ብሎ ለሹሞቹ እንደነገራቸው በጻፋቸው መጻሕፍት ገልጾታል።

ዘርዓ ያዕቆብ መንፈሳዊ እንደመሆኑ መጠን ከምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ከቁስጥንጥንያና ከእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት እየተዘጋጀ የወጣውን ሕግ በሲኖዶስ ያገኘውንም ሁሉ ለሀገሩ አብያተ ክርስቲያናት በትክክል ለማስፈጸም እንዲቻል በጽሑፍ እያባዛ ለካህናት በነፍስ ወከፍ እንዲዳረስ ማድረጉን ታሪክ ያስረዳናል፣ ዘርዓ ያዕቆብ የደረሳቸው መጻሕፍት ስማቸው ከላይ ተጠቅሷል በውስጣቸው ያዘኋቸው ምምስጢራት እንደሚከተሉት ናቸው ።

ተዓቅቦ ምሥጢር የሚባለው መጽሐፍ የሚናገረው ስለ ሚስጢረ ቁርባን ሲሆን መጽሐፈ ብርሃን የተሰኘው መጽሐፍ ደግሞ ከሁሉም የበለጠ በመሆኑ አንዳንድ ሊቃውንት በአድናቆት ይናገሩለታል ይህም መጽሐፍ አምልኮ ጣዖታትን በብርቱ የሚቃወምና ቅዳሜና ሌሎችም በዓላት በሚገባ መከበር ያለባቸው መሆኑን በሰፊው ይናገራል። እንዲሁም መጽሐፈ ምዕላድ የተባለው መጽሐፍ የጌታችን ልደት በየወሩ እንየሚከበርና በዚህ ዕለት የሚነበበውን እያስረዳ ከዚያም ይህንኑ መጽሐፍ ዘርዓ ያዕቆብ በየአብያተ ክርስቲያናቱ መላኩንና ሰው ሁሉ አምልኮ ጣዖትን ትቶ በእግዚአብሔር ብቻ እንዲያምን ያስገነዝባል መጽሐፈ ባሕር የሚባለው መጽሐፍ ስለኑዛዜና ስለ ቅብዓት ይናገራል ጦማረ ትስብእትም ከመጽሐፈ ብርሃን ጋር የተዛመደ ሆኖ ጠንቋዮችንና አስማተኞችን በብርቱ የሚያወግዝ ነው እግዚአብሔር ነግሠ ለቅዱሳንና ለሰማዕታት የተደረሰ ሰላምታ ነው። ከዚህ በላይ የተነገረው ብቻ አይደለም ።

ዘርዓ ያዕቆብ በዘመኑ የእመቤታችን ተአምር ከግብፅና ከኢየሩሳሌም አስመጥቶ ከዓረብኛ ቋንቋ ወደ ግዕዝ አስተርጉሞአል። መጽሐፈ ምሥጢር የተባለው መጽሐፍም የተጻፈው በእርሱ ዘመን ነው፣ የጊዮርጊስ ወልደ አሚድ መጽሐፍም ተጣርቶ የተጻፈው በዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነበር የቤተ ክርስትያን አባቶች ጳጳሳትና ካህናት ሊያስቡበትና ሊያሠሩት የሚገባቸውን የቤተ ክርስቲያንን ደንብና ሥርዓት እንዲሁም የቁርባንንና የጾምን የበዓላትን አከባበርና ሌሎችንም ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ ሕጐችና ደንቦች ሲያወጣ በመጽሐፍ ውስጥ ሁልጊዜ አተኩሮ በመመልከት የሚቃወመው አምልኮ ጣዖትን ነበር ።

ካላይ ስማቸው የተጠቀሰው መረዎችና ዘርዓ ያዕቆብ ከሥጋዊ ዳኝነት ተግባራቸው ጋር ስለ ሥነ ጽሑፍ ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ በመሆኑ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ



# የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ

## ትንቢተ፡ዳንኤል፡ ፰ ፡

እኔም፣ዳንኤል፣ራእዩን፣ባየሁ፣ጊዜ፣ማስ ፲፭፣
ተዋሉን፣ፈለግሁ፤እነሆም÷የሰው፣ምስያ፣
ቢሬቱ፣ቆሞ፣ነበር።በኡባልም፣ወንዝ፣መካ ፲፮
ከል፤— ገብርኤል፣ሆይ÷ራእዩን፣ለዚህ፣
ሰው፣አስታውቀው፣ብሎ፣የሚጮኸውን፣
የሰውን፣ድምፅ፣ሰማሁ ። እኔም፣ወደ፣ቆም ፲፯፣
ሁበት፣ቀረበ፤በመጣም፣ጊዜ፣ፈርቼ፣በግ
ምባሬ፣ተደፋሁ፤እርሱም፤— የሰው፣ልጅ፣
ሆይ÷ራእዩ፣ለፍጻሜ፣ዘመን፣እንደ፣ሆነ፣
አስተውል፣አለኝ ። ሲናገረኝም፣ደንግጬ፣ ፲፰፣
በምድር፣ላይ፣በግምባሬ፣ተደፋሁ፤እርሱም፣
ዳሰሰኝ፣ቀጥ፣አድርጎም፣አቆመኝ ። እንዲ ፲፱፣
ህም፣አለኝ፤— እነሆ÷በመቅሠፍቱ፣በመጨ
ረሻ፣ዘመን፣የሚሆነውን፣አስታውቅሃለሁ፤
ይህ፣ለተወሰነው፣ለፍጻሜ፣ዘመን፣ነውና ።

## ትንቢተ፡ዳንኤል ፱ ::

እኔም፣ገና፣ስናገርና፣ስጸልይ÷በኃጢአቴና፣ ፳፣
በሕዝቤም፣በእስራኤል፣ኃጢአት፣ስናዘዝ÷
በአምላኬም፣በእግዚአብሔር፣ፊት፣ስለ፣
ተቀደሰው፣ስለ፣አምላኬ፣ተራራ፣ስለምን÷
ገናም፣በጸሎት፣ስናገር፣አስቀድሜ፣በራእይ፣ ፳፩፣
አይቼው፣የነበረው፣ሰው፣ገብርኤል፣እነሆ፣
እየበረረ፣መጣ፤በማታም፣መሥዋዕት፣ጊዜ፣
ዳሰሰኝ ። አስተማረኝም÷ተናገረኝም፣እንዲ ፳፪፣
ህም፣አለ፤— ዳንኤል፣ሆይ÷ጥበብንና፣ማስ
ተዋልን፣እሰጥህ፣ዘንድ፣አሁን፣መጥቻለሁ።
አንተ፣እጅግ፣የተወደድህ፣ነህና፣በልመናህ፣ ፳፫፣
መጀመሪያ፣ላይ፣ትእዛዝ፣ወጥቶአል÷እኔም፣
እነግርህ፣ዘንድ፣መጥቻለሁ፤አሁንም፣ነገ
ሩን፣መርምር÷ራእዩንም፣አስተውል ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
ፖስታ ሣጥን ቍጥር 30755
አዲስ አበባ ።



www.ethiopianorthodox.org

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ | አ | ቡ | ጊ | ዳ | ጄ | ው | ዘ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ | በ | ጉ | ዲ | ሃ | ዌ | ዝ | ዠ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ | ገ | ዱ | ሂ | ዋ | ዜ | ዥ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ | ደ | ሁ | ዊ | ዛ | ዤ | ሕ | ጦ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ | ዐ | ዉ | ዚ | ዣ | ሔ | ጥ | ጮ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ | ወ | ዙ | ዢ | ሓ | ጤ | ጭ | ዮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ | ዘ | ዡ | ሒ | ጣ | ጬ | ይ | ኮ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ | ዠ | ሑ | ጢ | ጫ | ዬ | ክ | ኾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ | ሐ | ጡ | ጪ | ያ | ኬ | ኽ | ሎ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ | ጠ | ጩ | ዪ | ካ | ኼ | ል | ሞ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ | ጨ | ዩ | ኪ | ኻ | ሌ | ም | ኖ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ | የ | ኩ | ኺ | ላ | ሜ | ን | ኞ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ | ከ | ኹ | ሊ | ማ | ኔ | ኝ | ሶ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ | ኸ | ሉ | ሚ | ና | ኜ | ስ | ሾ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ | ለ | ሙ | ኒ | ኛ | ሴ | ሽ | ዖ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ | መ | ኑ | ኚ | ሳ | ሼ | ዕ | ፎ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ | ነ | ኙ | ሲ | ሻ | ዔ | ፍ | ጾ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ | ኘ | ሱ | ሺ | ዓ | ፌ | ጽ | ቆ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ | ሰ | ሹ | ዒ | ፋ | ጼ | ቅ | ሮ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ | ሸ | ዑ | ፊ | ጻ | ቄ | ር | ሦ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ | ዐ | ፉ | ጺ | ቃ | ሬ | ሥ | ቶ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ | ፈ | ጹ | ቂ | ራ | ሤ | ት | ቾ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ | ጸ | ቁ | ሪ | ሣ | ቴ | ች | ኆ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ | ቀ | ሩ | ሢ | ታ | ቼ | ኅ | ጶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ | ረ | ሡ | ቲ | ቻ | ኄ | ጽ | ፆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ | ሠ | ቱ | ቺ | ኃ | ጴ | ፅ | ፖ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ | ተ | ቹ | ኂ | ጳ | ፄ | ፕ | ጆ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ | ቸ | ኁ | ጲ | ፃ | ፔ | ጅ | ኦ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ | ኀ | ጱ | ፂ | ፓ | ጄ | እ | ቦ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ | ጸ | ፁ | ፒ | ጃ | ኤ | ብ | ጎ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ | ፀ | ፑ | ጂ | ኣ | ቤ | ግ | ዶ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ | ፐ | ጁ | ኢ | ባ | ጌ | ድ | ሆ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ | ጀ | ኡ | ቢ | ጋ | ዴ | ህ | ዎ |

ኰ ኵ ኲ ኳ ኴ
ጐ ጕ ጒ ጓ ጔ
ቈ ቍ ቊ ቋ ቌ
ኈ ኍ ኊ ኋ ኌ

ቨ ቩ ቪ ቫ
ቬ ቭ ቮ

፡ ፣ ፤ ። ? » ! / ) -

| ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፲ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | |
| ፳ | ፴ | ፵ | ፶ | ፷ | ፸ | ፹ | ፺ | ፻ | ፲፻ | ፼ |
| 20 | 30 | 40 | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 | 100 | 1,000 | 10,000 |

ሏ ሟ ሯ ሷ ሿ ቧ ቷ ቿ ኗ ኟ ዟ ዧ ዷ ጧ ጯ ጿ ፏ x



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ሳቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org